# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 354 ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

## መኖሪያ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞችና አረጋውያን አስረከቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በአዋሬ አካባቢ የተገነባ ባለ አራት ወለል የመኖሪያ ሕንፃን ለአቅመ ደካማ አባ ወራዎችና እማወራዎች አስረከበዋል።

በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት የተገነባው እና መኖሪያ ቤቶችንና የንግድ ሱቆችን ያካተተው ሕንፃ ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ትናንት ለተጠቃሚዎች ተላልፏል።

አንድ መንግሥት የራሱን ግቢና አካባቢ ካልቀየረ ሀገርን መቀየር አይችልም። ሁሉም ሰው ለውጥን ከአካባቢው መጀመር አለበት። በዚህ ዓመት በአቧሬ ለአቅመ ደካሞች እና ለአረጋውያን ያሠራናቸውን ቤቶች አስረክበናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር... ወደ ገጽ 8 ዞሯል








# «የሕዝብን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለይተን በቅደም ተከተል ለመፍታት እንሠራለን»

- አቶ አረጋ ከበደ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለይተን በቅደም ተከተል ለመፍታት እንሠራለን ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ

"የሕዝብን መሠረታዊ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# "አልወለድም" ያለው የደሴ ሆስፒታል

**በዳግማዊት ግርማ**

ይሠራል ከተባለ በኋላ ብዙ ሆኗል:: ከንቲባ መጥቶ ከንቲባ ሄዷል:: ደሴ ከአንድ እጅ ጣት ቁጥር በማያንሱ ሰዎች ተዳድራለች:: እነሱም ስፍራውን በመምራት ዘመናቸው ጎብኝተውታል:: እሱ ከታሰበ ወዲህ የተጸነሱ ልጆች ተወልደው ጎርምሰዋል:: አዝመራው አሽቷል:: የተዘራ በቅሏል:: ከዘጠናዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ስለሱ ይወራል:: በሁለት ሺህ አራት የመሠረት ድንጋዩ ተጥሏል::

ሆስፒታል ቢገነባ ሕመሜ ይፈወሳል ያለ ሁሉ ተረባርቧል:: በርካታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለድጋፍ ሲጠራ አቤት ብሏል:: ተቋሙን

"አልወለድም" ያለው... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



የወሎ ተርሸሪ ኬር ዲዛይን









# በአንድነት ከተሠራ ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን

## የአትሌቶቻችን ድል አድራጊነት ማሳያ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአንድነትና በመተባበር ስንሠራ ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን የአትሌቶቻችን ድል አድራጊነት ማሳያ ነው ሲል የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ::

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

በአንድነት ከተሠራ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል







ዜና

# በአማራ ክልል 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ተሠራጭቷል

## - ዩሪያ ማዳበሪያን በወቅቱ ለማድረስ ግን አልተቻለም

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ከሚያስፈልገው አምስት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ እስካሁን የተሠራጨው አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ:: ለአርሶ አደሩ ዩሪያ ማዳበሪያ በወቅቱ ማሠራጨት አለመቻሉንም ቢሮው አስታውቋል::

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አጀበ ስንሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው ለአርሶአደሩ የሚያስፈልገውን ግብዓት በወቅቱ ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው::

እንደ አቶ አጀበ ገለጻ የግብርና ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የግብዓት አቅርቦቱ ወሳኝ ነው:: ለክልሉ ከተገዛው አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ እስከ አሁን አራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታሉ መቅረቡን ተናግረው ከከረመው 299ሺ ኩንታል ጋር በማድረግ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለሥርጭት መቅረቡን ተናግረዋል::

እስከ አሁን አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወቅቱን ጠብቆ ለአርሶ አደሩ በአግባቡ መሠራጨቱንም ተናግረዋል::

ሆኖም የሚሠራጨውን ዩሪያ ማዳበሪያ መንገድ ላይ የማስቆምና የመንጠቅ ችግር አጋጥሞ ስለነበር በታሰበው ጊዜ ለአርሶአደሩ ማሠራጨት አዳጋች ሆኗል ብለዋል::

የጸጥታ መደፍረስ ችግር ካጋጠመ ጀምሮ ከ20 ሺ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ በመንገድ ላይና ከማኅበራት መዘረፉን የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው ዝርፊያ እየተፈጸመ በመሆኑ ባህር ዳር ላይ ወደተለያዩ ዞኖች የሚሄዱ 81 መኪኖች እንዲቆሙ መደረጉን ጠቁመዋል:: አጠቃላይ ችግሮችን ለመፍታትም ከክልሉ የጸጥታ ኮማንድ ፖስት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል::



ዩሪያ ማዳበሪያው ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎ እና ስንዴ ሰብሎች የሚውል እንደነበር የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው በትብብር መጠበቅ ሲኖርበት መዘረፉ የማይጠበቅና አሳዛኝ ተግባር መሆኑን ተናግረዋል::

በክልሉ 640ሺ ሄክታር መሬት ላይ የተዘራውና ከ35 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይሰበሰብበታል ተብሎ የታቀደው የበቆሎ ሰብል ዩሪያ ማዳበሪያ የመጀመሪያው ጊዜ እያለፈ መሆኑን ያስታወሱት አቶ አጀበ ዩሪያው በ15 ቀናት ውስጥ መሠራጨት ካልተቻለ የበቆሎ ምርት ሊቀንስ እንደሚችል አስረድተዋል::

ዩሪያ ማዳበሪያውን እስከ ጳጉሜ ወር ማድረስ ከተቻለ ሰብሉ ባለበት ሁኔታ እንዲጨመር በማድረግ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እንደሚጠቅምም ጠቁመዋል::

# ግንዛቤ የሚጎድለው የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

**ዓመለወርቅ ከበደ**

ማኅበራዊ ሚዲያን ዓለማችን መጠቀም ከጀመረች በርካታ ዓመታት ሊቆጠሩ ችለዋል:: ማኅበራዊ ሚዲያውም በኢኮኖሚው ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካው ዘርፍ ሕይወትን ቀላል አድርጓል:: በተቃራኒውም ያመጣቸው ተግዳሮቶችም አልጠፉም::

ኢትዮጵያም ከሠለጠኑ የዓለም ሀገራት ዘግይታ ማኅበራዊ ሚዲያውን ብትቀላቀልም፣ ማኅበራዊ ሚዲያውን መጠቀም ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል:: በእነዚህ ጊዜያቶች በማኅበራዊ ሚዲያው አማካኝነት የተፈጠሩ ጥሩ ዕድሎች ቢኖሩም፤ በዚያው ልክ ጥፋቶችና አንዳንድ መንገራገጮች አልጠፉም::

ኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሚዲያን እንዴትና ለምን መጠቀም እንዳለበት በቂ ግንዛቤ አለመኖሩ በተለይ ጥቅሙንና ጉዳቱን አለመገንዘቡ ከፍተኛ ቀውስ አስከትሏል ሲሉ በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ሥነ-ተግባቦት ትምህርት ክፍል ኃላፊ ወይዘሪት ዮርዳኖስ ግዛቸው ይገልጻሉ።

ማኅበራዊ ሚዲያ በኢትዮጵያ ባህልን፣ ቋንቋን ለዓለም ለማስተዋወቅ ብሎም የማኅበረሰብ እድገትን ለማምጣትና የቱሪዝም ፍሰትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና የተጫወተ ቢሆንም፤ በተቃራኒ ሀገሪቱን ለትልቅ ቀውስ ዳርጓል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ሰፊ ግንዛቤ ባለመኖሩ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

በተለምዶ ትኩረት የሚደረገው ላይክና ሼር በሚያድርጉ ላይ ብቻ ነው:: አንድ እኩይ መልዕክት የሚያስተላልፍ መረጃንና ሀሰተኛ ወሬን ማንበብ በእራሱ ያን መረጃ የሚያሰራጩ ሰዎች እንዲበረታቱ ያደርጋል:: በመሆኑም ሁሉም ዜጋ በሀገሩ ላይ ለሚፈጠረው ቀውስ ኃላፊነት አለበት ይላሉ።

በተለይ ወጣቱ ማኅበረሰብ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ስለሚያያቸው ነገሮች ለማን እንደተጻፈ፣ ለምን እንደተጻፉ፣ ለማን መረጃ እንደተለቀቀ በተጨማሪም፤ አይተው የተረዱትን ለማነው የማካፍለው የሚለው የግንዛቤ እጥረት እንዳለ ተናግረዋል::

የተማረውም፣ ያልተማረውም ፣ሚዲያ ላይ ያለውም ሆነ ከሚዲያ ውጪ ያለው በግንዛቤ የተሞላ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ባለማንሸራሸሩ ሀገሪቱ ቀውስ ላይ እንድትወድቅ አድርጓታል ሲሉ አስረድተዋል::

ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት የማኅበረሰብ ሚዲያውን በመጠቀም ባህላቸውን አስተዋውቀውበታል፣ የባንክ አገልግሎታቸውን እንዲዘምንና በሰዎች አስተሳሰብ ለውጥ ላይ እንደሠሩበት ይገልጻሉ::

ጉዳዩን ወደኢትዮጵያ ካመጣነው ግን እንዴትና ለምን እንጠቀም የሚለውን ማወቅ ብዙ ይጠበቅብናል ብለዋል።

አሁን ላይ በማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዱ አዳዲስ ሥልጠናዎች መስጠት መጀመራቸው ሚዲያ ላይ የሚሠሩ ሰዎችን መቀየር በራሱ ይህንን ችግር ለመፍታት እንደሚረዳ ነው የሚጠቁሙት::

መፍትሔው በመገናኛ ብዙኃን ለማኅበረሰቡ በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ በመስጠት፣ እውነታዎችን መርምሮ ለማኅበረሰቡ ለማድረስ እንደሚረዳ አመላክተዋል።

የማኅበራዊ ሚዲያው ነፃነት እየሰፋ በመጣ ቁጥር ችግሮች እየተከሰቱ ነው:: ስለዚህም ገደብ ቢኖረው ጥሩ ነው ያሉት ወይዘሪት ዮርዳኖስ፤ በሌሎች ሀገራት የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያ ላይ የተቀመጡ የሰዓት ገደቦች መኖራቸውን ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ 24 ሰዓት ተቀምጠው ሀሰተኛ ወሬን የሚያሰራጩ ስላሉ፤ ከቴሌኮም ድርጅቶች ጋር በመሆን ገደብ የማበጀት አሠራሮችን መፍጠር ይገባል ይላሉ።

በተጨማሪም እኩይ ተግባራትን የሚያሰራጩ ሰዎች የበይነመረብ አገልግሎታቸው መዘጋት ቢቻል ችግሩን በተቻለ መጠን ይቀንሰዋል ሲሉ ይገልጻሉ።

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ሥነ-ተግባቦት ትምህርት ክፍል መምህር አቶ ያለው ደሳለኝ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ማኅበራዊ ሚዲያ እንደ አረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻዎች ሲደረጉ ኅብረተሰቡን ለማሳተፍ ንቅናቄ ለመፍጠር ይረዳል።

ነገር ግን ተመሳሳይ ጥቅሞች እንዳሉት ሁሉ ሀሰተኛ መረጃንም ለማሰራጨትና ግጭት ለመፍጠርም አመቺ ቦታ ነው የሚሉት መምህሩ፤ ችግሩን ለመቀነስ የግንዛቤ ፈጠራው ላይ ይበልጥ ማተኮር ይገባል ባይ ናቸው።

በኢትዮጵያ አብዛኛው ማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ዕውነትንና፣ መረጃን አጣርቶ ያለመውሰድ ችግር ያለበት በመሆኑ የማኅበራዊ ሚዲያው ችግር እያስከተለ ነው ይላሉ።

መረጃ የሚያስተላልፈውም ሆነ የሚቀበለው አካል ተባለ በሚል ወሬ ነው የሚንቀሳቀሰው እንጂ ተጨባጭ መረጃን ለማግኘት ጥረት አያደርግም ሲሉ ገልጸዋል::

በማኅበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁት መረጃዎች ጥቅምን መሠረት ያደረጉ ሲሆን፤ በሚቀበለውም አካል፤ መረጃውን ተንትኖ እና አጣርቶ የመቀበል ጉድለት እንደሚታይ ነው የተናገሩት።

እንደመምህሩ ከሆነ፤ በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ፤ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች መደረግ ይኖርባቸዋል::

በተጨማሪም ሥልጠናዎችን ከታች ካሉት የትምህርት ክፍሎች ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች መስጠትና አስፈላጊውን የማኅበራዊ ሚዲያ ቁጥጥር ማከናወን እንደሚገባ ነው የገለጹት።

# በመዲናዋ

## ካሉት ከ187 ሆቴሎች የአደጋ ደህንነት መስፈርቱን ያሟሉት 23ቱ ብቻ ናቸው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ካሉት 187 ባለኮከብ ሆቴሎች የአደጋ ስጋት የደህንነት መስፈርቱን ያሟሉ ሆቴሎች 23 ብቻ መሆናቸውን የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የእሳት ማጥፊያ ሄሊኮፕተር ለመግዛት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ከአንድ እስከ አምስት የኮከብ ደረጃ በያዙ 187 ሆቴሎች ላይ የአደጋ ደህንነት መስፈርት ፍተሻ ተካሂዷል።

ፍተሻ ከተደረገባቸው 187 ሆቴሎች መካከል አስፈላጊውን የአደጋ ደህንነት መስፈርት ያሟሉ 23ቱ ብቻ ናቸው ብለዋል፡፡

ሆቴሎች አገልግሎትና ውበት ላይ ትኩረት አድርገው እንደሚሠሩ ጠቁመው፤ ወጪ ቅነሳንና ሌሎች ምክንያቶችን ታሳቢ በማድረግ ከዲዛይናቸው ጀምሮ የአደጋ ደህንነት መስፈርትን ሳያካትቱ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን አስረድተዋል።

ሆቴሎች የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ፣ የእሳት አደጋ ከመከሰቱ በፊት የሚያሳውቁ አንቂ መሣሪያዎች፣ የአደጋ መውጫ፣ ለድንገተኛ አደጋ መቆጣጠር የሠለጠነ ባለሙያ ያስፈልጋቸዋል፤ በተጨማሪ ሕንፃዎቻቸው የሚገነቡበት ግብዓት እሳትን ሊቋቋሙ የሚችሉ መሆን አለባቸው ብለዋል።

ይሁንና የተባሉት መስፈርቶች የማይገኙባቸው በርካታ ሆቴሎች በመኖራቸው ኮሚሽኑ የሆቴል ባለሙያዎችንና አመራሮችን ሰብስቦ አስፈላጊውን መረጃ እንዲደርሳቸው መደረጉን አመላክተዋል።

በአደጋ ስጋት ደህንነት የሚሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ ሰፊ ጥረት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሆቴሎች ማሟላት ያለባቸውን የደህንነት መስፈርቶች በተመለከተ በማዕከልና በዘጠኙም የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚገኙ ባለሙያዎች የቁጥጥር ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

ሆቴሎች እንደሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቀን አገልግሎት ሰጥተው ማታ የሚዘጉ ሳይሆን ደንበኞችን ቀንም ሆነ ማታ የሚያስተናግዱ የንግድ ተቋማት ናቸው ያሉት አቶ ንጋቱ፤ ሆቴሎቹ ለአደጋ ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ለደህንነት ያለው ትኩረት አናሳ መሆን፣ የውይይት መድረኮች ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ ያለመሆን፣ ክትትል ለሚያደርጉ ባለሙያዎች ተባባሪ ያለመሆንና በባለሙያዎች የሚሠጠውን ምክረሃሳብ ተግባራዊ አለማድረግ ለኮሚሽኑ ሥራ ተግዳሮት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የደህንነት መስፈርት ላሟሉ ሆቴሎች ዕውቅና የመስጠት፣ መስፈርቱን ለማሟላት እንቅስቃሴ ያልጀመሩት ላይ በሕጉ መሠረት ርምጃ መውሰድና መስፈርቱን ላላሟሉ ግንዛቤ መፍጠር እንዲሁም የክትትል ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በተያያዘ አዲስ አበባ ከተማ በርካታ ሕንፃዎችና በዙሪያዋ ጥብቅ ደኖች ያሏት ከተሟ በመሆኗ የአየር ላይ የእሳት አደጋ ማጥፊያ ያስፈልጋታል ያሉት አቶ ንጋቱ፤ የከተማ አስተዳደሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የእሳት ማጥፊያ ሄሊኮፕተር ለመግዛት የሚያደርገውን ዝግጅት ኮሚሽኑ በጋራ እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ አመራሮች በቀጣይ የእሳት ማጥፊያ ሄሊኮፕተሩ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ስለሚኖሩ ተያያዥ ሥራዎች በተመለከተ ከኢትዮጵያ አየር ኃይል ጋር በትብብር ለመሥራት ምክክር ማድረግ መጀመራቸውን አስታውቀዋል።

ምክክሩ የተለያዩ ቴክኒካል ድጋፎችን ለማግኘትና ሙያዊ ልምድ ለማግኘት እንደሚረዳ አመላክተዋል።

# በአረንጓዴ ዐሻራ ባለፉት ዓመታት 700 ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ባለፉት አምስት ዓመታት 700 ሺህ ለሚጠጉ ሰዎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በግበርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተፈራ ታደሰ፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እስካሁን በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግበር ወደ 700 ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፤ ይህንን የማሳደግ ሥራ ይከናወናል።

ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብርን አስጀምራ ወደሥራ ከገባች አሁን አምስተኛ ዓመት ላይ እንገኛለን ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ በእነዚህ ዓመታት የሀገር በቀል ችግኞች፤ የደን ተክሎች፣ ፍራፍሬዎች እና ሌሎች ተክሎች እንዲለሙ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ እስካሁን ባሉት ጊዜያት 30 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በዚህም ሂደት ከችግኝ ማፍላት፣ ከተከላ፣ ጉድጓድ ቁፋሮና በእንክብካቤ ሥራ እንዲሁም በተያያዥ ሥራዎች ላይ ዜጎች እንዲሳተፉ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ ተፈራ ገለጻ፤ በርካታ ዜጎች ለአረንጓዴ ዐሻራ የሚውል የእጽዋት ዘሮችን በማቅረብ፤ በችግኝ ጣቢያዎች ተቀጥረው በመሥራት የሥራ ዕድል አግኝተዋል፡፡

በተጨማሪም ችግኞችን በመሸጥና የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ገቢያቸውን ያሳደጉ ዜጎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ በርካታ ሥራ አጥ ወጣቶች እንደመኖራቸው በቀጣይም በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብሮች ሰፊ የሰው



ኃይል በማሰማራት የሥራ ዕድል ፈጠራውን ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል።

ከአረንጓዴ ዐሻራ የፍራፍሬ ችግኞች አሁን ላይ ማፍራት በመጀመራቸው ተጨማሪ ገቢ መፍጠር እንደተቻለም ገልጸዋል።

አቶ ተፈራ እንደተናገሩት፤ በአረንጓዴ ዐሻራ በመርሐ ግብር የሚተከሉት የፍራፍሬ ችግኞች የአካባቢን አረንጓዴነትን ከመጠበቅ በተጨማሪ፤ በሀገሪቱ በምግብ መቀንጨር ወይም የተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚጥማቸውን ዜጎች ሕይወት በመታደግ ረገድ ጉልህ ድርሻ እንደሚወጡ ይታመናል።

ገበሬው ፍራፍሬውን ከመመገብ በተጨማሪ፤ በመሸጥ ገንዘብ ያገኝበታል ይህም ለሥራው ተነሳሽነት እንዲኖረው ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የፖለቲካ አመራሩ መነሳሳት፣ የኅብረተሰቡ ፈቃደኛነት፣ የሀገሪቱ ሥነምህዳርና የዓለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ ለአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ስኬት ምቹ ዕድል ፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ተፈሪ ገለጻ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት የአካባቢ ጥበቃ የካርበን ሽያጭ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሥራዎች ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር እየተከናወነ ይገኛል።

# በአውደርዕዩ የቀረቡ ቴክኖሎጂዎች ለትራንስፖርት ዘርፉ ጥራት ያለው መረጃ ማድረስ ያስችላሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአውደርዕዩ የቀረቡ የውሃና ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ለትራንስፖርት ዘርፉ ጥራት ያለው መረጃ ማድረስ ያስችላሉ ሲሉ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር አለሙ ስሜ ገለጹ።

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር አመራርና ሠራተኞች «የውሃ ሀብታችን ለብልጽግናችን» በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን አውደ ርዕይ ትናንት ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ዶክተር አለሙ ስሜ እንደተናገሩት፤ በውሃና ኢነርጂ አውደ ርዕይ የቀረቡት ቴክኖሎጂዎች ለትራንስፖርት ዘርፉ ጥራት ያለው መረጃን በብቃት ማድረስ የሚያስችሉ ናቸው።

አውደ ርዕዩ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በቴክኖሎጂ ታግዞ እየሠራቸው ያሉትን ሥራዎች የሚያስቃኝ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህም የአየር ሁኔታን በሳይንሳዊ መንገድ መግለጽ ከሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች፣ ደመና ማበልጸግና ከትራንስፖርት ዘርፍ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የሚያቀርቡ ሳይንሳዊ ምርምር ሥራዎች መቅረባቸውን አመላክተዋል።

የትራንስፖርት ዘርፍ በምድር ብቻ ሳይሆን በአየር ያለውንም እንደሚያጠቃልል ጠቁመው፤ ቴክኖሎጂዎቹ ለትራንስፖርት ዘርፉ ጥራት ያለው መረጃን በብቃት በማድረስ ለዘርፉ ውጤታማነት የሚያግዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በሚቲዮሮሎጂና በውሃ ዙሪያ የሚከናወኑ ሥራዎች ለትራንስፖርት ዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

አውደ ርዕዩ በውሃና ኢነርጂ ዘርፍ ሀገሪቱ የደረሰችበት ቴክኖሎጂ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን የማድረግ ጉዞ አመላካቾች ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ለኢትዮጵያ ብልጽግና እያንዳንዱ ሴክተር የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተሰጠውን ሀገራዊ ኃላፊነት እየሠራ ያለው ሥራ የሚያስደንቅ ነው። በተለይ በታዳሽ ኢነርጂ ኢትዮጵያውያንን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ ያለው ሥራ ሊበረታታ የሚገባ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን ጋር በሳይንስ ሙዚየም የውሃና ኢነርጂ አውደ ርዕይ በይፋ የከፈቱ ሲሆን የኢትዮጵያን እምቅ የውሃ እና ኢነርጂ ሀብት ለዜጎች ለማሳየት ዓላማ ያለው አውደ ርዕዩ ከነሐሴ 13 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለጎብኚዎች ክፍት መሆኑ ይታወቃል።

# የሀገራዊ ምክክር ተሳታፊዎች አካታችና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ይለያሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክር ተሳታፊዎች አካታችና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንደሚለዩ የተሳታፊ ልየታ ተባባሪ አካላት ገለጹ፡፡

የምክክሩን ተሳታፊዎች ለመለየት የሚያስችል በቂ ሥልጠና ማግኘታቸውን ከአዲስ አበባ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተወከሉ ተባባሪ አካላት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ተሳታፊ ልየታ ተባባሪ የሆኑት መላከገነት አዕምሮ መልካሙ የሀገራዊ ምክክር የተሳታፊ ልየታን ለማድረግና አጀንዳ ለማሰባሰብ የሚረዳ ሥልጠና እንደተሰጣቸው ገልጸው፤ ነፃና ገለልተኛ በመሆን መንገድ የተሳታፊ ልየታ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል።

በሥልጠናው አማካኝነት የተፈጠረልንን ግንዛቤ ይዘን ከአካባቢያችን ሕዝብ ጋር በስፋት እንወያያለን ያሉት መላከገነት አዕምሮ፤ ተሳታፊዎችን አካታችና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለይተን በሕዝቦች መካከል አንድነት፣ መረዳዳት፣ መግባባትን ለማዳበርና ልዩነቶችን ለማጥበብ እንሠራለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሴት ስትወልድ አዋላጅ፣ ሰው ሲታመም ሐኪም እንዲሁም ሰው ሲቸገር ረዳት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ሀገር ችግር ውስጥ በገባችበት ወቅት ምክክር ማድረግ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ይገባል ብለዋል።

ብሔራዊ ምክክሩ ሲደረግ ደግሞ ወጣቱን፣ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ነጋዴውን፣ ቅሬታ ያለውን ጨምሮ ሁሉንም ማኅበረሰብ ባካተተ መልኩ ማከናወን እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በመሆኑም የመንግሥት ሠራተኛውንም ሆነ የግል ተቀጣሪውን እንዲሁም ሥራ አጡንም ጭምር በአጠቃላይ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሊወክሉ የሚችሉ ተሳታፊዎችን በቀጣይ እንለያለን ሲሉ ተናግረዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያውያን ቁጭ ብለው በመነጋገርና በመግባባት በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ አንድነትና ዕድገት እንዲፈጠር መሥራት አለባቸው ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሌላኛው በሀገራዊ ምክክር የተሳታፊ ልየታ ተባባሪ የሆኑት የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ ጀማል መሐመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የእኔ ብቻ ይሰማና እኔ ያልኩት ይሁን በሚል ሃሳብ ግጭት ይፈጠራል፡፡

ለችግሮቻችን መፍትሔው ደግሞ ያሉንን አጀንዳዎች ወደሀገራዊ ምክክሩ በማቅረብ መደማመጥና በሰከነ መንፈስ መወያየት ነው ብለዋል።

በምክክሩ ሁሉም ዜጋ በአንድ ጊዜ መሳተፍ ስለማይችል የተመረጡ ተሳታፊዎችን ወክሎ ማቅረብ ደግሞ ደንብ ነው ያሉት አቶ ጀማል፤ ፍትሐዊና አካታች በሆነ መንገድ ተሳታፊዎችን በውይይት ለመምረጥ መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል።

በምክክሩ የሚሳተፉ አካላት የተወከሉበትን የማኅበረሰብ ክፍል ጥያቄና ችግር በአግባቡ የሚያቀርቡ፣ ሃሳባቸውን መግለጽ የሚችልና ስለሚወክሉት ኅብረተሰብና ጥያቄ በቂ ግንዛቤ ያላቸው መሆን እንዳለባቸው በመረዳቴ፤ በሥልጠናው መሠረት ልየታ አደርጋለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከፍተኛ ባለሙያና የተባባሪ አካላት አሠልጣኝ አቶ ጥበቡ ታደሰ በበኩላቸው፤ የሀገራዊ ምክክር ምንነትን፣ ለምክክሩ የተከናወኑ ዝግጅቶችንና ቀጣይ አቅጣጫዎች እንዲሁም አካታችና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዴት ተሳታፊዎችን መለየት ይቻላል? በሚል ርዕስ ለተሳታፊ ልየታ ተባባሪ አካላት ሥልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ደረጃ ከመምህራን ማኅበር፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከዕድሮች፣ ከወረዳ አስተዳደር፣ ከሲቪክ ማኅበራትና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወከሉ ተባባሪ አካላት በቂ የሥልጠናና የግንዛቤ ፈጠራ መድረኮች መከናወናቸውን አመላክተዋል።

ከተባባሪ አካላት ጋር በትብብር ይሠራል ያሉት አቶ ጥበቡ፤ ኮሚሽኑ በተሳታፊዎች ልየታም ሆነ በቀጣይ ሥራዎቻቸው ላይ ክትትል፣ ቁጥጥርና እገዛ ያደርግላቸዋል ብለዋል።



መላከገነት አዕምሮ መልካሙ



አቶ ጀማል መሐመድ



አቶ ጥበቡ ታደሰ

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራዊ ምክክሩ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብሩህ ነገ መሠረታዊ ነገር ነው !

ኢትዮጵያውያን በሀገራችን ህልውና ለመጣ ቀልድ አያውቁም። ቤቴ፣ ርስቴ፣ ሚስቴና ልጆቼ ሳይሉ ሀገራችንን አስቀድመው ራሳቸውን ለመስዋዕትነት ያቀርባሉ።

በደምና አጥንታቸውም ሉዓላዊነታቸውን ያስከብራሉ፤ ነጻነታቸውንም ያረጋግጣሉ። አልፎ ተርፎም በኮሪያ፣ በኮንጎ፣ በላይቤሪያ፣ በሶማሊያ፣ በሩዋንዳና ብሩንዲ እንዲሁም በሱዳን በመዝመት በግጭትና በጦርነት ውስጥ የገቡ ሀገራትን አረጋግተው ወደ ሰላማቸው መልሰዋል።

ሆኖም የጀግንነታችንና ለሌሎች ሀገራት ጭምር የነጻነት ተምሳሌት የመሆናችን ያህል የውስጥ ሰላማችንን በማረጋገጥ ግን ብዙም አልተሳካልንም። በጀግንነትና በሰላም ማስከበር የገዘፈ ታሪክ ያለንን ያህል በሰላም የመኖር ጥበብ ርቆን ብዙ ተቸግረናል። የኢትዮጵያን ታሪክ መለስ ብሎ ላየው የውስጥ አለመግባባት፣ ግጭትና ጦርነት የበዛበት ነው። ተነጋግረን መፍታት በምንችላቸው ጉዳዮች መነጋገርና መግባባት ሳንችል በግጭትና ጦርነት ውድ ዋጋ ከፍለናል።

ይህ ደግሞ ሀገሪቱን በማያባራ ግጭትና ጦርነት ውስጥ ከቷል፤ ለበርካታ ሰዋዊና ቁሳዊ ኪሳራም ዳርጓል። ለሀገሪቱ ዕድገትም ፈተና ሆኗል። ይህ የታሪካችን አንዱ ክፋይ ግን አንድ ቦታ መቆም አለበት። የግጭት፣የጦርነት፣ ያለመግባባት ታሪካችን ተዘግቶ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ የምንግባባ፤ ለጋራ ሀገራችን የምንተጋ፤ ለልጆቻችንም የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማውረስ የጋራ ዕሳቤ የጨበጥን አዲስ ትውልድ መሆን ይገባናል።

ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በምክክርና በመግባባት ነው። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባትም እንደሀገር የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ አንድ ዓመት ከስድስት ወራት አስቆጥሯል። በእነዚህ ጊዜያትም ምክክሩ የሚመራበትን አቅጣጫ ከመቀየስ ጀምሮ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮዎችን የመቀመርና በምክክሩ የሚሳተፉ ሰዎችን የመለየት ሥራዎች ተከናውነዋል። በቀጣይም የምክክሩን አጀንዳዎችን ከኅብረተሰቡ የመቀበልና ምክክሩን ወደ መሬት የማውረድ ሥራዎች ይከናወናሉ።

ስለሆነም ሀገራዊ ምክክሩ የቀድሞ ችግሮቻችን፣ አሁን ያሉት ችግሮቻችን መፍቻና በቀጣይም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳያጋጥሙን የመፍትሔ አቅጣጫን የሚጠቁመን መሠረታዊ ነገር መሆኑን ማመን ይጠበቅብናል።በሀገሪቱም መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረትም እርሾ ሆኖ እንደሚያግዝ እምነት መጣል አለብን።

ለዚህም ሁሉም ነገር በንግግር እና በምክክር ይፈታል የሚል እምነት ማዳበር ይጠበቅብናል። ወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በሀገራዊ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም።

አሁን እዚህም እዚያም ያሉት አለመግባባቶች ተወግደው በፍቃደኝነት እና በመግባባት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ምክክሩ የማይተካ ሚና አለው። ሀገራዊ ምክክሩ ከዘመን ወደ ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን የመፍታት፣ የመወያየትና የመነጋገር ባህልንም ለማዳበር ይረዳል። በመወቃቀስ ላይ የሚያተኩረውንም የፖለቲካ ባህላችንን ወደ መነጋገር፤ መተባበርና መደጋገፍ እንዲመጣ ያደርጋል።

ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል። ከመነጋገር ይልቅ ለንትርክ አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል። አሁን ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፣ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው።

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደ ሀገር ሊኃሰብበት ይገባል። የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና። በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት። የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው። ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣልን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል። በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፣ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው።

ስለሆነም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን አለመግባባትንና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፣ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል በሚገባ ልንጠቀምበት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልተሻገርናቸውን የትናንት ችግሮች ተነጋግሮ ለመሻገር

ከትዝታ ማስታወሻ

ምእራባውያን ‹‹ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም›› (Rome wasn't built in a day) የሚሉት አባባል አላቸው። ትልቅ ነገር የአንድ ቀን ውጤት ሳይሆን በሂደት የሚመጣ ነው ለማለት የሚጠቀሙበት አባባል ነው። እኛም ዘንድ ተመሳሳይ ነው፤ የአክሱም ሐውልት፣ የፋሲል ቤተመንግሥት፣ የሐረር ግንብ ሌሎችም በአንድ ቀን አልተፈጠሩም።

ከማሰብ እስከ መገንባት በርካታ ቀናትን አለፍ ሲልም ዓመታትን ወስደዋል። አዲስ ነገር ለመገንባት አንድ ቀን በቂ አይደለም፤ የተገነባን ለማፍረስ ግን አንድ ቀን ሊበቃ ይችላል። ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን ለመውደዳችን ማንንም እማኝ መጥራት አያሻም። ለዘመናት የተለያዩ ትውልዶች ስለሀገራችን የከፈሏቸው መስዋእትነቶች ለዚህ ህያው ምስክሮች ናቸው። የሀገር ጉዳይ ገፍቶ ሲመጣም እንደ ሕዝብ ያለን መነሳሳት ሌላው ማሳያ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገራችን ላለፉት ዘመናት አንድ የሚያደርገን ነገርን በጋራ አክብረን፤ የተናጠል ልዩነታችንን ውበት መሆኑን ይዘን ከመቀጠል ይልቅ በዳይና ተበዳይ በሚል መቧደን ምርጫችን ሲሆን ተስተውሏል። ይህ ደግሞ የተማሩ ተብለው የፖለቲካ ቦታ ባገኙ ሰዎች ይበልጥ መቀንቀኑ ችግሩን ይበልጥ የከፋ አድርጎታል።

አንድ በሚያደርገን የአትሌቲክስ ድል እንኳን ብሔር እየቆጠሩ ወደመደሰት ተሸጋግረናል። በጋራ ለሀገር አንድነት አብረው የዘመቱ ጀግኖችን ወደኋላ ተመልሰን እነሱ ያልለበሱትን የብሔር ካባ መደረብ ምርጫችን ሆኗል።

በሰዎች መካከል ትክክለኛ ተግባቦት ለመፍጠር አንድ ብሔር እንዲህ ነው ብሎ አስቀድሞ መፈረጅ ተገቢም ልክም አለመሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። ግን በሀገራችን አንዱን ጠባብ፣ አንዱን ትምክህተኛ፣ አንዱን ተስፋፊ እያልን የዳቦ ስም እየሰጠን ዳቦ ሳንቆርስ አለን።

ድሮም አሁንም አፈር ገፊ የሆነው አብዛኛው ሕብረተሰብ አሁንም በኑሮው ላይ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ የለም። ዳሩ ‹ነገዬን ብሩህ ያደርጉልኛል› ብሎ ጥሪቱን ሸጦ ሳይማር ያስተማራቸው ልጆቹ የአሁኗን ኢትዮጵያ ከመኖር ይልቅ የድሮዋን ኢትዮጵያ ጉድለቶች ማስታወስ ምርጫቸው አድርገዋል።

ትናንት የተዘራ መርዝ ለዛሬ እንደተረፈ ሁሉ ዛሬ የሚዘራ መርዝ መዘዙ ከዛሬ ይሻገራል። ትውልድ በታሪክ አጋጣሚ መልካምም ሆነ መጥፎ እድል ይሰጠዋል። የአሁኑ ትውልድ ስለድሮውም ሆነ ስለአሁኑ በደቂቃ ውስጥ የፈለገውን ምላሽ የሚያገኝበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ችግሩ ቴክኖሎጂውን አለመፍጠራችን ሳያንስ፤ የተፈጠረውን ማኅበራዊ ሚድያ በተገቢው መልኩ መጠቀም አለመቻላችን ነው። የደበረውና ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ያሰበ ሁሉ፤ ከእውቀት ነጻ በሆነ መልኩ ሰዎችን ሲሳደብ አንዱን በአንዱ ላይ ሲቀሰቅስ የሚያስተላልፋቸው መልእክቶች ሰዎች የተሻለ ተጨንቀውና አስበው ከሚሰሯቸው መልዕክቶች የተሻለ ተመልካች ያገኛሉ።

አሁን አሁንማ የመገናኛ ብዙኃንም ለእንግድነት ከሚያቀርቧቸው አብዛኞቹ ሰዎች በተለያዩ ማኅበራዊ ሚድያዎች በኩል ከሕዝቡ ጋር የተዋወቁ መሆን ከጀመሩ ሰነበቱ። ሀገር ሰላም ሁሉ አማን ሲመስል ዋነኛ ትኩረታችን ዳንኪራ መደለቅ ይሆናል። አለፍ ሲልም የሀገሪቷን ሕዝቦች የተለያዩ እንደሆኑ አንዱ አንዱን ሲበድል እንደነበር ይወሳል።

ያም ቢሆን ሀገር ተወረረች ሲባል ሁሉም ለሀገር ሰላም በአንድነት ዘብ ይቆማል። ሆኖም በሰላም ጊዜም አንዱ በአንዱ ላይ ያለውን ቂም ሲያውጠነጥን ከሚከርም ለሀገር አንድነትና እድገት በጋራ ብንሰራ ዛሬያችንም ነጋችንም መልካም ይሆናል።

ሌሎች ሀገራት የትናንት መጥፎ ጠባሳቸውን በጋራ አክመው ተሻግረውታል። ከተለያዩ ሀገራት እንደ እንስሳ አካላቸው ተገምቶ በዋጋ የተሸጡ ዜጎች ልጆች በዳዮቻቸውን ይቅር ብለዋል።

የትናንት ተበዳዮች ሁሉን ትተው ስለዛሬያቸውና ስለነጋቸው ዛሬን በትጋት መሥራት መርጠዋል። እኛ ስለአያት ቅድመ አያቶቻችን ሥራ ዛሬን እንገዳደላለን። የዛሬ መገዳደል ደግሞ ለነገ ቂም ያስቋጥራል።

በርካቶች ዛሬን ከመኖር ይልቅ ምርጫቸው ስለድሮው ማውጠንጠን ሆኗል። ችግሩ የድሮውን ዘመን አሁን ባለን አረዳድ መመዘናችን ነው። ለምን ልክ እንደኛ አላሰቡም? ለምን እንደኛ አልሆኑም? ብለን ስንብሰለሰል ለእኛ የተሰጠን ዘመን ሳንጠቀምበት ባክኖ ይቀራል። ፉክክራችን ከሞተና ካለፈ ሥርዓት ጋር ሲሆን አሁን ያሉት ይበልጥ ጥለውን ይሄዳሉ።

እኛ የድሮዎቹ ‹እንዲህ ቢያደርጉ› ኖሮ ብለን ስንቆጭ እኛ ማድረግ ያለብንን ማድረግ ሳንችል ቀርተናል። እስከመቼ ያለፉትን ወቅሰን እንዘልቃለን? ዓለም ምድር ጠቧት ሰዎች ስለአማራጭ መኖሪያዎች ይጨነቃሉ። እኛ አሁንም ሃሳባችን ከቀበሌዬ ውጣ፤ ቅድመ አያትህ አያቴን አሰቃይቶታል ላይ ተቸክሎ ቀርቷል። ለመሆኑ በዚህ ዓይነት እሳቤ እስከመቼ ድረስ እንቆዝማለን?!

በደሉን ያልናቸውን ቀደምቶቻችንን እንብለጣቸው፤ እኛ ከእነሱ ተሽለን ለነገ ትውልድ የተሻለች ሀገር ማቆየት ላይ እናተኩር። በያዝንበት ከቀጠልን የዛሬ ሂሳብ አወራራጆች ነገ ሂሳብ ይወራረድባቸዋል። ይሄ አዙሪት አንድ ቦታ ካልተሰበረ ድግግሞሹ ሀገርንም ሕዝብንም ወደኋላ ያስቀራል።

ለመጪው ትውልድ ከብቀላ አዙሪት በመውጣት ርግማንን ሳይሆን ምርቃት ማሻገር ላይ መስራት ይጠቅመናል። ለዚህ እስካሁን ብንዘገይም በፊታችን ባለው ሀገራዊ ምክክር መድረክ እውን ልናደርገውና ዘመን ተሻጋሪ ለሆኑ ችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሄ ልናገኝ እንችላለን።

# ፍረዱኝ

# የተቋማት አለመናበብ፤ የመረጃም ድብብቆሽ የበረታበት- የመሬት ክፍፍል

ሙሉቀን ታደገ እና ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**መነሻ ጉዳይ**

**ጉዳዩ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ስለሚስተዋለው የመሬት ወረራ እና አግባብ ያልሆነ የመንግሥት ሀብት ቅርምት ብሎም የመንግሥት ተቋማት ያልተናበቡበት አሠራር ስለመኖሩ ከአካባቢው ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን ጥቆማ አደረሱ፡፡ ዝግጅት ክፍሉም የነዋሪዎቹን ጥቆማ መነሻ በማድረግ በሥፍራው በመገኘት ሁኔታውን ተመልክቷል፤ የነዋሪዎቹን አስተያየት፣ ሰነዶች እና የሚመለከታቸውን አካላት አነጋግሮም ጉዳዩን እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡**

## ነዋሪዎች ምን አሉ?

ለዝግጅት ክፍላችን ጥቆማውን ያደረሱ እና ለደህንነታቸው ሲሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ የአካባቢ ነዋሪዎች፣ በአካባቢያቸው እየሆኑ ያሉ ነገሮች ሁሉ እንግዳ ሆነዋል። በአካባቢያቸው ለአርሶ አደር ልጅ እየተባለ እየተከናወነ የሚገኘው ተግባርም በእጅጉ አሳዛኝ ነው ብለዋል። “አርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጆች ናቸው” በሚል ምክንያት ለግለሰቦች የተመራው ቦታ አግባብነት የጎደለውና በአካባቢው ያልነበሩ ሰዎች የተከፋፈሉት ፍንትው ያለ ሙስና የጎላበት ተግባር ስለመሆኑ ገልጸዋል።

ዝግጅት ክፍሉ በስፍራ ተገኝቶ እንደተመለከተው፣ የአካባቢ ማህበረሰብ በጋራ ከኪሱ ገንዘብ በማዋጣት የሠራው የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ‹‹ኮብል ስቶን›› ሳይቀር በአሁኑ ወቅት ተቆፍሮ ግለሰቦች ግንባታ እያካሄደበት ነው።

ቀደም ሲል በዚህ የኮብልስቶን የመንገድ ዳር እናቶች የጉሊት ችርቻሮ ንግድ ሲያከናውኑ፣ የእግረኛ መንገድ ዘግታችኋል በሚል ሰበብ በደንብ አስከባሪዎች እንዲነሱ መደረጉን የሚገልጹት የአካባቢው ነዋሪዎች፤ በሂደት አሻጥር በመፍጠር ለአርሶ አደር ተሰጥቷል በሚል ግንባታ እንዲከናወንበት የተደረገ መሆኑን ነው ያስረዱት።

ከዚህ በተጨማሪም ለቅርምት የተዳረጉት ቦታዎች ቀደም ሲል አረንጓዴ ቦታ የነበሩ ቦታዎች በአካባቢው ማህበረሰብ በጋራ የለሙና በተመሳሳይ በጋራ ይጠቀሙበት የነበሩ ናቸው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት የፕላን ተቃርኖ የለውም በሚል ሰበብ ለግለሰቦች በመስጠት ግንባታ እየተካሄደበት ነው። ነዋሪዎቹ ግን ይህ በሐተሰኛ መረጃዎች የታጨቀ ነው፤ በአካባቢው ፈጽሞ ያልነበሩ ሰዎች እንደኖሩ ተደርጎ ሊሰጥ አይገባም ሲሉ ቅሬታቸውንና ተግባሩን የሚቃወሙ መሆኑን አስረድተዋል።

የፕላን ተቃርኖ የለም የሚለው ከሞራልም ሆነ ከእውነት የራቀ ነው የሚሉት ነዋሪዎቹ፤ የእግረኛ መንገድ ሙሉ ለሙሉ ታጥሮ እስከ አስፋልት ጥግ ድረስ እየተቆፈረ ነው። ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ ምሰሶዎችን በግንባታዎቹ ጣሪያ ላይ የሚያልፉ ናቸው። ታዲያ ይህን የፕላን ተቃርኖ የለውም ማለት ከእውነትም፤ ከዕውቀትም ብሎም ከሞራል የራቀ ይልቁንም ለሙስና የተጋለጠ አሰራር ስለመሆኑ ተናግረዋል።

## ”አርሶ አደሮች ነን‘ የሚሉ ግለሰቦች ምን አሉ?

ምንም እንኳን ይህ የሰላ ወቀሳና ትችት ከአካባቢ ነዋሪዎች የቀረበ ቢሆንም፤ “የሚባለው ሁሉ ውሸት ነው” በማለት አርሶ አደሮች ነን የሚሉት ግለሰቦች ሃሳቡን ተቃውመው ሃሳባቸውን ገልጸውልናል። ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል ደግሞ ወይዘሮ አስናቀች ዳባ አንዷ ናቸው።


ወይዘሮ አስናቀች ዳባ፤ ለብዙ ዘመናት ለግብርና አገልግሎት ስንጠቀምበት የነበረው መሬታችን ያለ አግባብ ሲወሰድና ስንፈናቀል ኖረናል። ይህንንም አቤት ለማለት በየፍትህ ተቋማቱ በር እየዞርን ስንጮህ ነበር፤ ግን ሰሚ አላገኘንም። ይሁንና አሁን ድምፃችን ሲሰማና ምላሽ ማግኘት ስንጀምር የማይመለከታቸው አካላት እየከሰሱን ነው፤ ብለዋል።

እኛ የአካባቢው አርሶ አደሮች አሁን የተወሰነ አንገት ማስገቢያ የሚሆን ቦታ ሲሰጠን አያስገርምም የሚሉት ወይዘሮ አስናቀች፤ ይሄ እንዲሆንም ለዘመናት ዋጋ የከፈልንበት ነው፣ ገናስ መቼ በቂ ፍትህ አገኘንና ብለዋል። ከ100 ዓመት በፊት ቅድመ አያቶቻችን ጭምር ይኖሩበት የነበረ ቦታ በመሆኑ፣ በእኛ ላይ እየተነሳ ያለው ተቃውሞ አግባብነት የጎደለውና ፍትህ እንዳይነግስ ከመፈለግ የመጣ ነው ሲሉ በነዋሪዎቹ የቀረበውን ቅሬታ ተቃውመዋል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ አቶ መብራቴ ስንታየሁ በበኩላቸው፤ አካባቢው ከጥንት ጀምሮ የኖርንበት ሲሆን ሌላው ቀርቶ በአያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ስም የሚጠሩ ሰፈሮችና የምንጮች ስም አሁንም ድረስ ያሉ ህያው ምስክር ናቸው ይላሉ። እንዲያውም አሁን ለመኖሪያ ተብሎ የተሰጠን ቦታ ሊሰጠን ከሚገባው በእጅጉ ያነሰ ለዘመናት የተነፈግነውን መብታችንን ‹‹ዓባይን በጭልፋ›› ዓይነት ነው የተሰጠን ሲሉ አሁንም ቅሬታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

ሌላው ቀርቶ በአካባቢው የጋራ መኖሪያ ቤቶች በገዛ መሬታችን ላይ ተገንብተው ለነዋሪዎች ሲተላለፉ የበይ ተመልካች ሆነን ኖረናል፣ ያሉት አቶ መብራቴ፤ በአሁኑ ወቅት ካርታ የተሰጠን በጉልበት ወይንም በሙስና ሳይሆን ከቀጣና ጀምሮ በወረዳ፣ ክፍለ ከተማ እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ድረስ በተዋቀሩ ሕጋዊ ኮሚቴዎችና መንግሥታዊ የሥራ ኃላፊነት ላይ በተቀመጡ ሰዎች ተረጋግጦ ነው ብለዋል።

ይሁንና ለዘመናት ዋጋ የከፈልንበት ጉዳይ በእኛ ያላሰለሰ ጥረትና በመንግሥትም ይሁንታ ፍትህ እያገኘን መሄዳችን አሁንም የማይዋጥላቸው ግለሰቦች ዱካችንን እየተከተሉ የተሳሳተ መረጃ እየሰጡ ነው፤ እነሱ ምንም ቢሉ “እኛ በአካባቢው የተወለድን ብሎም ነባር አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ልጆች ነን” ብለዋል።


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ
የነባር ባለይዞታነት ማረጋገጫ
የምስክር ወረቀት

16
Addis Ababa City Government Land Development and Administration Bureau
Title Deed Certificate for Old Possession

የባለይዞታው ሙሉ ስም / Possessor's Full Name: አቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ
ሴሪ ቁጥር:- № 07235079 / Serial
የቤዝ ማፕ ቁጥር / Base Map No.: AK 14/51 -
የመዝገብ ቁጥር / Registration Book No.: 1
የምዝገባ ተራ ቁጥር / Registration No.: 1098
የካርታው ቁጥር / Title Deed No: 14/02/1/1098
ካርታው የተሰጠበት ቀን / Date of Issued: 02/10/2015

የባለይዞታው ፎቶግራፍ



የቦታው ማገናኛ ነጥቦች Coordinates

| X | Y |
|---|---|
| 465873.40 | 1001317.07 |
| 465863.79 | 1001324.64 |
| 465862.42 | 1001322.85 |
| 465862.99 | 1001315.14 |
| 465858.56 | 1001317.79 |
| 465853.97 | 1001311.77 |
| 465864.70 | 1001304.31 |

አዋሳኞች

| | |
|---|---|
| ሰሜን (N) | |
| ምስራቅ (E) | |
| ደቡብ (S) | |
| ምዕራብ (W) | |

ሚዛን: 1:500 / Scale

| ክ/ከተማ Sub city | ወረዳ Wereda | የብሎክ ቁጥር Block No. | ፓርሴል ቁጥር Percel No. | የቤት ቁጥር House No. | ግንባታ ያረፈበት የቦታ ስፋት /Built up/ | የቦታው ስፋት /Plot Area/ | የቦታው ደረጃ Land Grade | የቦታው አጠቃቀም Land use Plan | የቤቱ አገልግሎት Function of the House |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አዲስ ከተማ | 14 | 5 | - | - | 120.25 | 183.68 | 2-1 | Low Density Mixed Residence | ለመኖሪያ |

የቴክኒክ አጣሪና ካርታ አዘጋጅ ባለሙያ: ይደነቅ እንዱዓለም 01/10/2015 ዓ.ም
የሰነድ አጣሪ ባለሙያ: 01/10/2015 ዓ.ም
ያፀደቀው ኃላፊ: 1/10/15 ዓ.ም

## የወረዳ 14 ዋና ሥራ አስፈፃሚ ምላሽ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ድሪባ ጉልማ እንደሚሉት፤ በዚህ አካባቢ የሚነሱ ቅሬታዎች በሕግ አግባብ የተከናወኑ ናቸው። ከአቶ ፍቃዱ ዳባ በስተቀር ሁሉም ሰዎች መብት የተፈጠረላቸው ከሁለት ዓመት በፊት ነው። መብት የተፈጠረውም “አርሶ አደር” እና “ምትክ” በሚል ነው። ሊታወቅ የሚገባው ግን በአርሶ አደርም ይሁን በምትክ ስም የመሬት ጉዳይ ለወረዳ የሚመጣው ከክፍለ ከተማ ነው።

በመሆኑም መጀመሪያ ላይ ካርታ አውጥተው የመጡት ከክፍለ ከተማ ነው። ወረዳው የሚሰራው ከሰነድ አልባ ጋር የተያያዘን ጉዳይ ብቻ ነው። በሰነድ አልባ መብት ይፈጠርልኝ የሚሉ ሰዎችን ፋይል አደራጅተን መብት እንዲፈጠርላቸው ወደ ክፍለ ከተማ እንልካለን እንጂ ከአርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጅ ጋር ተያይዞ ወረዳ ላይ የሚሰራ የለም፤ ብለዋል።

ይሄንን ምላሻቸውን መነሻ በማድረግ እና መመሪያ ቁጥር 20/2013ን ዋቢ በማድረግ፤ “በአርሶ አደርነት የይገባኛል ጥያቄ ሲነሳ መጀመሪያ በቀጣና ኮሚቴ ታይቶ፤ በወረዳው መሬት ልማትና ማኔጅመንት አስተዳደር ተገምግሞ ለወረዳው ሥራ አስፈጻሚ ሲቀርብ እና ሥራ አስፈጻሚው ካጸደቀው በኋላ ክፍለ ከተማ ለአርሶ አደሮቹ መብት ይፈጥርላቸዋል። አሰራሩ ይህ ሆኖ ሳለ እንዴት ከአርሶ አደር ጋር ተያይዞ ወረዳው የሚያውቀው ነገር የለም ይላሉ?” የሚል ጥያቄ ከዝግጅት ክፍላችን የቀረበላቸው አቶ ድሪባ፤ መጀመሪያ ላይ ወረዳው አያገባውም ያሉ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን አርሶ አደር እና የአርሶ አደርን ልጅ በተመለከተ የይገባኛል ጥያቄ መስተንግዶ ከወረዳ እንደሚጀምር አምነዋል።

አርሶ አደር ለተባሉት ሰዎች የተሰጠው መሬት አለ ስለተባለው ጉዳይም፣ ‹‹ሁሉም ቦታዎች የፕላን ተቃርኖ አያሳዩም›› ሲሉ ነው አቶ ዲሪባ ምላሽ የሰጡት። ካርታው ተሰርቶ የመጣው ከክፍለ ከተማ መሆኑን፤ ክፍለ ከተማ ቦታውን ጠቅሶ ካርታ ከሰራላቸው ደግሞ ምንም እንኳን በቤታቸው ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ተሸካሚ መስመር ቢያልፍም ወረዳው ምንም የማድረግ መብት እንደሌለውም ተናግረዋል።

“የወረዳ 14 ነዋሪዎች ይገለገሉበት የነበረ የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ ‹‹የኮብል ስቶን›› መንገድ አርሶ አደር ናቸው ለተባሉ ግለሰቦች በምሪት ተሰጥቷል። ሕዝብ እና መንግሥት ለመንገድ ብሎ ወጪ ያወጣበትን መሠረተ ልማት ለቤት ግንባታ መስጠት ተገቢ ነውን?” ተብለው የተጠየቁት አቶ ድሪባ፤ ቦታው በኮብል ስቶን መንገድ እንዳልተሰራበት ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ ዝግጅት ክፍሉ ስለቦታው በፎቶ ማስረጃ እንዳለው ሲገልጽላቸው፤ መንገዱ በፕላን ላይ አይታይም የሚል ሌላ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህን መልሳቸውን ተከትሎ ቦታው በፕላን ባዶ ቦታ የሚያሳይ ከሆነ ለእግረኛ የኮብል ድንጋይ ንጣፍ ሲሰራ ለምን አልከለከላችሁም ለሚለው ጥያቄ ግን ምላሽ መስጠት አልቻሉም።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በአቶ ፍቃዱ ስም የተመራው እና ግንባታ የተጀመረበት ቦታ ቀደም ሲል ካርታ ተሰርቶለት የመከነ ነበር። አሁን ላይ እንደገና ነው ካርታ የተሰራለት። ግንባታ በሚካሄድበት ቦታ ደግሞ ኮብልስቶን መንገድ የነበረ ነው። ዝግጅት ክፍላችንም ይሄንን በሰነድም በአካልም ተመልክቷል።

ይሄን አስመልክቶ የኮብል ስቶን መንገድ የለም ብለው ሲከራከሩን የነበሩት ሥራ አስፈጻሚው፤ ከአስፋልት ዳር የእግረኛ መንገድ አለ፤ ከእግረኛ መንገዱ ቀጥሎ ስለሆነ ኮብል ስቶን መንገዱ የተነጠፈው ለምን ይጠቅማል? ሲሉ ራሳቸው ጠያቂ ሆነው ቀርበዋል። እኛም ጥያቄአቸውን በጥያቄ መልሰን ኮብል ስቶኑ የማይጠቅም ከሆነ ከጅምሩ የመንገዱ ግንባታ ሕገወጥ ነበር? ስንል ጠየቅናቸው። ሥራ አስፈጻሚውም ‹‹ሕገ ወጥ ነው አላላኩም›› የሚል ምላሽ ሰጥተውናል። ሆኖም ጥያቄ ከሚመስል ምላሻቸውም ጭምር መረዳት እንደሚቻለው በቦታው ላይ የኮብልስቶን መንገድ የነበረ መሆኑን ነው።

ቦታውን የወሰዱት እና ቦታው ይገባቸዋል በማለት ውሳኔ ያስተላለፉት የቀጣና ኮሚቴዎች በትክክል አርሶ አደሮች ናቸው? የወረዳው ነዋሪዎች ናቸው? ለሚለው ጥያቄም ሥራ አስፈጻሚውም ‹‹አዎ የወረዳው ነዋሪዎች ናቸው›› ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ያለ አግባብ ለቤተክርስቲያን በአስፋልት ዳር ለዚያውም 200 ካሬ የማይሞላ ቦታ ላይ እንዴት ፈቃድ ሊያገኝ ቻለ? የሚል ጥያቄ ለዋና ሥራ አስፈፃሚው ያነሳንላቸው ሲሆን፤ ዋና ሥራ አስፈፃሚውም ይሄ የሆነው ቦታውን ከተመሩት አርሶ አደሮች ተከራይቶት እንጂ በምሪት ተሰጥቶት አይደለም ብለዋል።

ይሁንና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፤ ቤተክርስቲያኑ ከመስጅድ ጎን በመሆኑ የጸጥታ ችግር እንዳያስከትል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ወስኖ የሰጣቸው ቦታ ነው የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

ከገጽ 6 የዞረ

# የተቋማት አሰመናበብ...

### የክፍለ ከተማው ምላሽ

አቶ አንዱአለም ይጥና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ናቸው። እንደ አቶ አንዱአለም ይጥና ገለጻ፤ በ2013 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ምርጫ ነበር። የ2013 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ የአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር የራሱ የሆነ መቋቋሚያ አዋጅ አዘጋጀ። ይህ መቋቋሚያ አዋጅም ቁጥር 74/2014 ይባላል።

በዚህ አዋጅ መሠረት ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ሥር የነበሩ አራት ወረዳዎች ወደ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እንዲካተቱ ሆነ። አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ እነኝህን ወረዳዎች ከኮልፌ ከቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ሲረከብ አርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጆች ጋር ተያይዞ የነበሩ ባለጉዳዮች መረከባቸውን ያስረዳሉ። ከተረከቧቸው አርሶ አደሮች መካከለም 40 ለሚሆኑት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መብት ተፈጥሮላቸው ነበር ይላሉ።

ነገር ግን የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር መብት በተፈጠረላቸው አርሶ አደሮች ላይ ምርመራ ካደረገ በኋላ 22 የሚሆኑትን ካርታዎች እንዲመክኑ ማድረጋቸውን ይናገራሉ። ለዚህም በምክንያትነት ያነሱት አንድ ሰው አርሶአደር በተመለከተ ሊስተናገድ የሚችለው መመሪያ ቁጥር 20/2013 በመሆኑ ነው።

በዚህ መመሪያ ሦስት ዋና ዋና ጭብጦች አሉ የሚሉት ኃላፊው ፤ አንደኛ፣ አሁን ላይ አርሶ አደሩ መሬቱ በእጁ ያለና የሚጠቀምበት ከሆነ መብት ተፈጥሮለት ይስተናገዳል። ሁለተኛ፣ ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው ቦታ የፕላን ተቃርኖ ቢኖረውም ይስተናገዳል። ለምሳሌ፣ አረንጓዴ ስፍራ ወይም የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሊሆን ይችላል። ይህን መሰል የፕላን ተቃርኖ ሲኖር መሬቱ ለአርሶ አደሩ ልጅ ወጪ ተደርጎ እንደሚሰጥ በመመሪያው ተቀምጧል። ሦስተኛው፣ በ1997 እና 1988 የአየር ካርታ ላይ የማይታይ ቢሆንም ይስተናገዳል የሚል ነው።

እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ጭብጦች መሠረት በማድረግ የሚደርሷቸውን ጥቆማዎች ለማጣራት ክፍለ ከተማው ከተማ አስተዳደሩ ጋር በመሆን የኦዲት ግብር ኃይል ማቋቋማቸውን ይገልጻሉ። የተቋቋመው የኦዲት ግብር ኃይልም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ብቻ 22 የሚጠጉ በሕገ ወጥ የተወሰዱና ካርታ የተሰራላቸውን ቦታዎች ማግኘቱን ጠቁመው፤ የ22ቱም ካርታ እንደመከነ እና መሬቱም ወደ መሬት ባንክ እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል። 18 የሚሆኑት ደግሞ ግብረ ኃይሉ ማጣራት ካደረገ በኋላ እንዲጸድቅ ተድርጓል።

በመመሪያ ቁጥር 20/2013 በአንቀጽ 9 እንደተመላከተው ደግሞ መብት እንዲፈጠርላቸው የጠየቁ ሰዎች አርሶ አደር እና የአርሶአደር ልጅ ስለመሆናቸው ሲጣራ ኮሚቴ ይቋቋማል። ኮሚቴውም የወረዳውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የወረዳው ግብርና ኮሚሽን፣ የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፣ እንዲሁም አርሶ አደሩን የሚያውቁት የቀጣና ኮሚቴዎች የያዘ ነው። 18 የሚሆኑት መብት የተፈጠላቸው አርሶ አደሮችም በመመሪያው መሠረት ሕጉን ጠብቀው የተስተናገዱ ስለሆነ ግብረ ኃይሉ ጥያቄአቸውን አጽድቆታል። ይሁን እንጂ አሁንም በወረዳው የተለያዩ ቅሬታዎች እንደሚነሱ አመልክተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርምራ ክፍል አርሶ አደር ተብለው መሬት የተሰጣቸው ሰዎች የአካባቢው ማኅበረሰብ በጋራ አልምቶ ሲጠቀምበት የቆየውን የኮብል ስቶን መንገድ መሆኑን ከኅብረተሰቡ ጥቆማ ደርሷል። እናም በቦታው ተገኝተን ሁኔታውን አረጋግጠናል። ስለዚህ ምን ይላሉ ብሎ ለኃላፊው ጥያቄ ተነስቶላቸው ነበር። ኃላፊውም፣ የለማ ኮብል ስቶን መንገድ ለአርሶ አደር በሚል መሰጠቱን እንደማያውቁ ገልጸው፤ ስለጉዳዩ በማጣራት ለዝግጅት ክፍሉ ስለሁኔታው እንደሚገልጹ ተናግረዋል።

2.6. “ብሎክ አደረጃጀት” ማለት በመንገድ ወይም በወንዝ ወይም በጅረት ወይም በእርሻ ቦታ ወይም በመሳሰሉት በተከለለ አካባቢ አርሶ አደሮች ያሉበት አደረጃጀት ነው፤

2.7. "ኮሚቴ" ማለት በወረዳዉ ረጅም ዓመት የኖረና በአርሶ አደሩ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሆነው የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚመለከተው አካል ጋር በኃላፊነት መንፈስ እንዲሰሩ በአርሶ አደሮቹ የተመረጡ ሰዎች የሚገኙበት የአርሶ አደር ኮሚቴ ነዉ፤

2.8. “አርሶ አደር” በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በከተማ ግብርና ስራ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ ራሱንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ሰው ነው፤

2.9. “የአርሶ አደር ልጅ” ማለት የአርሶ አደር ልጅ ስለመሆኑ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና መረጃ ጽህፈት ቤት የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት ወይም ልጅ ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ሰው ነው፤

2.10. “በአርሶ አደር የተያዙ ይዞታዎች” ማለት በከተማው አስተዳደራዊ ወሰን ዉስጥ አርሶ አደሩ ለተለያዩ የከተማ ግብርና ሥራዎች እና ለመኖሪያነት እየተጠቀመበትና እያስተዳደረዉ ያለዉ መሬት ነዉ፤

2.11. “የከተማ ፕላን” ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈጻሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን የፕላኑ አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤

**ከመመሪያው 2003 የተወሰደ**

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 በአርሶ አደር እና በአርሶ አደር ልጅ ስም የተሰጣቸው መሬት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ተሸካሚ ገመድ የሚያልፍባቸው፤ ትልልቅ የኃይል ተሸካሚ ፖሎችም ያሉበት ነው። እንደዚህ ዓይነት ከባድ የኃይል ተሸካሚ መስመሮች በያዙ ቦታዎች እና የፕላን ተቃርኖ ያለባቸው ቦታዎችን መስጠቱ ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ? ቦታው የተሰጡት ሰዎች አርሶ አደር ናቸው ቢባል እንኳን ከባድ የኃይል አስተላላፊ ገመድ በሚያልፍበት አካበቢ መሬት መስጠት ለሚደርሰው አደጋ ተጣያቂው ማን ነው ሲል ዝግጅት ክፍሉ ጠይቋል።

አቶ አንዱአለም በምላሻቸው፤ በመመሪያ ቁጥር 20/2013 መሠረት ለአርሶ አደር የሚሰጡ ቦታዎች የፕላን ተቃርኖ ቢኖርባቸውም ለአርሶ አደሮች እንዲሰጡ ያዝዛል።

ይህ ብቻ ሳይሆን 1988 ዓ.ም ጂ.አይ.ኤስ እና 1997 ላይን ማፕ ላይ ባይታይም እንኳን ለአርሶ አደሮች እንዲሰጥ መመሪያው ያዝዛል ያሉት ኃላፊው፤ ሆኖም መመሪያው የራሱ ድክመት እና ጥንካሬ ስለሚኖረው ይሄን መተቸት እንደማይፈልጉም ጠቁመዋል።

ሌላው በዝግጅት ክፍሉ ለኃላፊው ከተነሱ ጥያቆች መካከል፣ በወረዳው አርሶ አደር ከተባሉት አካላት በተጨማሪ የህይወት ምንጭ ዓለም አቀፍ ቤክርስቲያን ተገንብቷል። ስለዚህ ምን የሚያውቁት ነገር አለ? የሚል ነበር። ለጥያቄው ምላሽ የሰጡት ኃላፊው፤ በወረዳው የብድር መስጅድ እና ቤተክርስቲያኑ ጎን ለጎን ነበሩ። ይህ ደግሞ በሁለቱ አማኞች መካከል የጸጥታ ስጋት የመፍጠር ዕድል ይኖረዋል።

ይህን ተከትሎ ባለፈው ዓመት የከተማ አስተዳደሩ ባስቀመጠው የ60 ቀን እቅድ የሁለቱ ቤተ ዕምነቶች ካልተነጣጠሉ ለወረዳውም ብሎም ለክፍለ ከተማ እንዲሁም ለከተማ አስተዳደሩ የጸጥታ ችግር እንዳለው በመረዳት የከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መጥተው ጉዳዩን ከተመለከቱ በኋላ ቤተክርስቲያኑ እንዲነሳ በማድረግ አሁን ቤተክርስቲያኑ የሚገኝበት ቦታ መሰጠቱን አመልክተዋል።

በእርግጥ አሁን ቤተክርስቲያኑ የሚገኝበት ቦታ ግማሽ አረንጓዴ ስፍራ፣ ግማሹ «ሪዚደንስ» ነበር የሚሉት ኃላፊው፤ ሆኖም በቦታው የፕላን ማሻሻያ መደረጉን ተናግረዋል። በዚህም ቤተክርስቲያኑ በፊት ከነበረበት ቦታ መነሳቱን ገልጸዋል። ኃላፊው ይሄን ይበሉ እንጂ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባደረገው ማጣራት ቤተክትርስቲያኑ እስካሁን ከቦታው አለመነሳቱን ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ የአካባቢው ነዋሪዎች ተናግረዋል።

በተጨማሪ ለቤተክርስቲያኑ የተሰጠው መሬት ሂደቱን ጠብቆ በከንቲባ እና መሬት ልማትና ማኔጅመንት አምኖበት እንደተሰጠ ኃላፊው ቢገልፁም፤ የወረዳ 14 ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች እንደገለጹት፤ ቦታው ለቤተክርስቲያኑ በምሪት አለመሰጠቱን ተናግዋል። ይሄም ሌላው የተቃርኖ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ተችሏል።

ይህ ቤተክርስቲን ባረፈበት ቦታ የመብራት ኃይል ተሸካሚ ፖሎች እና ገመዶች የሚያልፉበት ነው። ይህን ጉዳይ እንዴት አያችሁት? ተብለው የተጠቁት ኃላፊው፤ «የኤሌክትሪክ ኃይል ተሸካሚ ገመድ መኖሩን አላየሁትም» የሚል ምላሽ ሰጥተውናል። ኃላፊው አክለውም የኤሌክትሪክ ገመዱን በተመለከተ ማንም ሰው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ ጉዳዩን ለኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በማሳወቅ የኃይል ተሸካሚው ምሰሶ እንዲነሳና ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወር ለማድረግ እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

### የኤሌክትሪክ አገልግሎት ምላሽ

ምሰሶው በሚያልፍባቸው ቦታዎች ላይ ሕንፃዎችን መገንባት ይቻላል ወይ? ቤት የሚገነቡ ካሉስ ተቋማችሁ መብቱን እንዴት ያስጠብቃል? ተብለው የተጠየቁት የምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪክት ቁጥር1 ሥራ አስኪያጂ አቶ ወንድወሰን ፈዬራ እንደገለጹት፤ መሬት የሚሰጠው ሌላ አካል ነው። የመብራት ኃይል የሚሰራው የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ብቻ ነው። መስመር ከተዘረጋ በኋላ ቤቶች ቢገነቡ የቤት ግንባታ ጋር የሚያገናኘው አካል ነው መጠየቅ ያለበት እንጂ የእኛ ተቋም አይደለም። ሆኖም መስሪያ ቤቱ በሰዎች መኖሪያ ቤት ላይ ከባድ ኃይል ተሻካሚ ገመድ መዘርጋት ይቅርና በአጥር ላይ እንኳን ዝቅተኛ ኃይል ተሻካሚ ገመድ አይዘረጋም ብለዋል።

ከቤቶች ግንባታ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት መመሪያ ምን ይላል? ተብለው የተጠየቁት አቶ ወንድወሰን፤ መጀመሪያ የኃይል ተሸካሚ መስመር ተዘርግቶ ከነበር እና በኃይል ተሸካሚው ገመድ ስር ግንባታ ማከናወን የሚፈልግ ሰው በመመሪያው መሰረት ማዘዋወሪያ ይጠይቃል። ለማዘዋወሪያው ክፍያ ይከፍላል። በመቀጠልም የኃይል ተሸካሚ መስመር ማዘዋወር ግዴታቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

በዚህ አግባብ ለሚመጡ ሰዎች የማዘዋወር ሥራ እየሠራን ነው ነው የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፤ አሁን ውዝግብ በተነሳበት ቦታ ግን ማንም አካል ጥያቄ ለተቋማቸው እንዳላቀረበና ስለጉዳዩም ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዝግጅት የምርመራና መልካም አስተዳደር ክፍል መስማታቸውን አስረድተዋል።

ይህን ተከትሎ አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ክፍል ጋዜጠኞች እናንተ ሳታውቁት እንደዚህ አይነት ግንባታ ሲካሄድ መስሪያ ቤታችሁ ምን ዓይነት እርምጃ ይወስዳል? ተብለው የተጠየቁት አቶ ወንድወሰን፤ መሰል ችግር ሲያጋጥም በቅድሚያ ችግሩ ለተፈጠረበት ወረዳ ጉዳዩን በማሳወቅ ግንባታ ያካሄዱት አካላት ሕጋዊ ስለመሆናቸው ያጣራል። በመቀጠልም በቦታው ችግር ቢከሰት መሥሪያ ቤታቸው ተጠያቂ እንደማይሆን በማሳወቅ አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጠው ለወረዳው ያሳውቃል። ችግሩ በወረዳው የማይፈታ ከሆነ ጉዳዩን ወደ ተቋማቸው ህግ ክፍል በመውሰድ በሕግ አግባብ እንዲታይ እንደሚደረግ ያስረዳሉ። ሆኖም አሁን ላይ ውዝግብ በተፈጠረበት ቦታ ችግር ቢከሰት መሥሪያ ቤታቸው ስለጉዳዩ ስለማያውቅ በማንኛውም መንገድ መጠየቅ እንደማይችል አመልክተዋል።

*መመሪያው ምን ይላል?*

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር የመኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 20/2013 መሰረት፤ በክፍል አንድ በተቀመጠው ጠቅላላ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር 2.8 እንደሚለው «አርሶ አደር ማለት» በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በከተማ ግብርና ሥራ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ ራሱንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ሰው ነው ይላል።

በተጨማሪም ንዑስ ቁጥር 2.10 «በአርሶ አደር የተያዙ ይዞታዎች» ማለት በከተማው አስተዳደራዊ ወሰን ውስጥ አርሶ አደሩ ለተለያዩ የከተማ ግብርና ሥራዎችና ለመኖሪያነት እየተጠቀመበትና እያስተዳደረው ያለው መሬት ነው ይላል። በዚሁ ክፍል ቁጥር 4 ላይ የተቀመጠው የተፈፃሚነት ወሰን በተመለከተ ደግሞ፤ ይህ መመሪያ በከተማው ክልል ውስጥ በአርሶ አደር እና በአርሶ አደር ልጆች ለመኖሪያ እና ለተለያዩ የግብርና ሥራዎች አገልግሎት እየሰጡ ባሉ የመሬት ይዞታዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚል ነው።

ምንም እንኳን መመሪያው ይህን ቢልም፤ ለረጅም ዓመታት የኖሩ አካባቢ ማኅበረሰብ መሬት ላይ ያለው እውነታ ከዚህ የተለየ መሆኑን ያስረዳሉ። ከወረዳውና ከሥራ ኃላፊዎች የተገኘው መረጃም እነዚህ ግለሰቦች ይህ ስፍራ ትክክለኛ ይዞታቸው ነው የሚል መረጃ ማቅረብ አልቻለም።

### ሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም መረጃዎችን ለማጥራት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 በተደጋጋሚ ቢመላለስም በቂ ማስረጃ ማግኘት አልቻለም። በወረዳው ሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት እነዚህ ግለሰቦች በወረዳው ነዋሪዎች ስለመሆናቸው መረጃዎችን ለማየት የሞከረ ሲሆን፤ ግለሰቦቹ የአካባቢው ነዋሪ ስለመሆናቸው ብሎም በቦታው ላይ ግብርና እያካሄዱ ነበር የሚል መረጃ አላገኘም። በአብዛኞቹ ግለሰቦች ሥም የተመዘገበ መታወቂያ ሊያገኝም አልቻለም።

በመሆኑም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የምርመራና መልካም አስተዳደር ክፍል በቀጣይ አባሪ መረጃዎችን በማከልና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ «እውነት ከየት እንደሆነች» ለአንባቢያን አስፈላጊውን መረጃ የሚያደርስ ይሆናል።

# የዲጂታል ዕውቀትን ለሰላም ግንባታ መሣሪያነት መጠቀም ይገባል

በዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የዲጂታል ዕውቀትን ለሰላም ግንባታ መሣሪያነት መጠቀም እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት እና ሜታ (ፌስቡክ) ያዘጋጁት በኢትዮጵያ የሰላም ግንባታ ሂደት የዲጂታል መድረክ ዕድሎችና ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

በመርሐግብሩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የፕሮግራምና ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ሃና ወልደገብርኤል እንደገለጹት፤ ምክር ቤታቸውና ሜታ የዲጂታል እውቀት በኢትዮጵያ የሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ቁልፍ መሣሪያ እንደሆነ ለማስተዋወቅ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው።

የሲቪል ማኅበረሰቡ የቴክኖሎጂና የዲጂታል መድረኮችን በመጠቀም በሰላም ግንባታ ዙሪያ ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላል ተብሎ ይታሰባል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ማኅበረሰቡን በማስተማርና በማንቃት ጤናማ የዲጂታል መድረኮች አጠቃቀም እንዲኖር መሥራት አለባቸው ብለዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ የዲጂታል ዕውቀትን በመጠቀም ማኅበረሰቡም እራሱን ከአሉታዊ ተፅዕኖዎች መጠበቅ ይኖርበታል። ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት በመሥራት ሀሰተኛና አሉታዊ መረጃዎችን ማጋለጥ ያስፈልጋል።

የሜታ (ፌስቡክ) የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሕዝብ ፖሊሲ ዳይሬክተር ሜርሲ ንደጓ በበኩላቸው፤ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ኃላፊነት የሚሰማው የዲጂታል መድረክ አጠቃቀምን በማጎልበትና በመረጃ የተደገፈ፣ ትርጉም ያለውና ውጤታማ ተሳትፎን መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

ድርጅታቸው ከኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አስፈላጊውን የዲጂታል ክህሎት ለማስያዝ የሚረዳ መድረክ ማዘጋጀቱን አመላክተዋል።

የሰላም ግንባታ ጥረቶች በማጠናከር የዲጂታል መድረኮች ገንቢ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል መሥራት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የዲጂታል ግንኙነት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ውጤታማ የሰላም ግንባታ ስትራቴጂዎችን የመንደፍ አቅምን ያሳድጋል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ግንኙነቱን እያጠናከሩ ለተሻለ ውጤት መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የማኅበራዊ ትስስር ሚዲያዎችን በመጠቀም በኅብረተሰቡ ውስጥ ለውጥና ሽግግርን ለማምጣት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ እንዳሉ ሁሉ አላግባብ በመጠቀም የተሳሳቱ መረጃዎች የሚያሰራጩ አካላት መኖራቸውን አንስተዋል።

የአመፅ ጥሪዎችና የጥላቻ ንግግሮች እንዲበራከቱ እንዲሁም አላስፈላጊ ጉዳቶችን እንዲደርሱ በማባባስ ትልቅ ፈተና የሚፈጥሩ አካላትን በጋራ መከላከል እንደሚገባ በመድረኩ ተመላክቷል፡፡

ለሁለት ቀናት በሚካሄደው የሥልጠና መርሐ ግብር የክልል ተሳታፊዎች እንዲሁም ከአዲስ አበባ የተውጣጡ 40 የሲቪል ማኅበራት እየተሳተፉ ይገኛል።

የሥልጠና መርሐ ግብሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ተወካዮችን ኃላፊነት በተሞላበትና ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ የዲጂታል መድረኮችን አጠቃቀም ዕውቀታቸውን ለማሳደግ ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

# በአንድነት ከተሠራ ውጤቱ ያማረ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢትዮጵያ በሀንጋሪ ቡዳፔስት ከተማ በተካሄደው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ያስመዘገበችውን ድል አስመልክቶ መግለጫ አውጥቷል፡፡

በመግለጫው እንደተጠቀሰው፤ የቡዳፔስቱ መድረክ የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ እንደወትሮው ሁሉ ከፍ ብሎ የተውለበለበበት መድረክ ነው፡፡

ከድሉ ባሻገር የነበረው የቡድን ሥራ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ያኮራና አንጸባራቂ ድል እንደነበርም በመግለጫው ተነስቷል፡፡

«አረንጓዴው ጎርፍ» እየተባለ የሚጠራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን፤ ዘንድሮም ስያሜውን በሚመጥን መልኩ አትሌቶቻችን ተከታትለው በመግባት የሀገራችንን የድል ታሪክ ደግሟል ሲል በመግለጫው አመላክቷል።

በተለይ በሴቶች 10 ሺህ ሜትርና በማራቶን ሩጫ የታየው የቡደን ሥራ፣ እርስ በእርስ መናበብና መረዳዳት ከድል ምክንያትነቱ ባሻገር ኢትዮጵያውያን ስንተባበር ተዓምር መሥራት እንደምንችል ያሳየ ነው ብሏል፡፡

አትሌቶቻችን በሩጫ ወቅት መረጃ በመለዋወጥ፣ በመተጋገዝ እና አንዳቸው ሌላውን በመጠበቅ እስከመጨረሻው ድረስ በቡድን መጓዛቸው የሚደነቅ እንደሆነም በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

ሀገራችን በውድድሩ ሁለት የወርቅ፣ አራት የብርና ሦስት የነሐስ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ከዓለም ስድስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ሁለተኛ ሆና ውድድሩን በማጠናቀቅ በቀጣይ ዓመት ለሚደረገው የኦሎምፒክ ውድድር ስንቅ የሚሆኑ ተሞክሮዎች የተገኙበት ነው ሲል አገልግሎቱ አስታውቋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአትሌቲክስ ውድድሮች ጠፍቶ የነበረው የኢትዮጵያውያን የቡድን ሥራ በዘንድሮው ውድድር በጉልህ መታየቱ በዘርፉ ያለንን ስኬት በቀጣይ ጊዜያት ለማሻሻል የሚያስችል እንደሆነም ገልጿል፡፡

ከምንም በላይ ከውጤቱ ባሻገር ውጤቱ የተገኘበት መንገድ ኢትዮጵያውያንን በጋራ ያስደሰተ፤ የሀገራዊ አንድነታችን ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ አኩሪ ድል መሆኑ በመግለጫው ተነስቷል፡፡

ሀገርን በተለያዩ ዓለምአቀፍ መድረኮች በመወከል ድል ማስመዝገብ የሚወደስ ተግባር ነው ያለው አገልግሎቱ ሀገራችን ከጊዜያዊ አሉታዊ ፈተናዎች ባሻገር በተለያዩ ዘርፎች ድል የሚያደርጉ የትጉሃን ሀገር መሆኗን ለዓለም ማሳየት በሁሉም ዘርፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አገልግሎቱ ገልጿል።

ኢትዮጵያ በጥረታቸው ድል የሚያደርጉ፣ የሀገራቸውን መልካም ገፅታ አጉልተው የሚሳዩ የብርቅዬ ልጆች ቤት መሆኗ ዛሬም በዓለም አደባባይ ታይቷል ሲልም በመግለጫው አመላክቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከፈተናዋ በላይ ተስፋዋ የለመለመ፣ አዎንታዊ ስኬቷም በእጅጉ እንደሚልቅ በተለያዩ ዘርፎች እየታየ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

በስፖርት ዘርፉ ከትውልድ ወደ ትውልድ የቀጠለው የአሸናፊነት ገድል በቀጣይ ጊዜያትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም በትብብር ሊሠራ እንደሚገባ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መልዕክት አስተላልፏል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአስከፊ ሁኔታ በፈራረሰ ቤት ውስጥ ኑሯቸውን ይገፉ የነበሩት እና አዲሱን ቤታቸውን የተረከቡት እማ ወራና አባ ወራዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና መንግሥታቸው ለተሻለ ሕይወት ያደረጉላቸው ድጋፍ እንዳስደሰታቸው በመግለጽ ምስጋና አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በመደመር ትውልድ መጽሐፋቸው ገቢ ለአቅመ ደካማ አባ ወራዎችና እማ ወራዎች ያስገነቡት ባለ አራት ወለል ሕንፃ የንግድ ሱቆችን እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡባቸው ስፍራዎችን ያካተተ ነው።

# «የሕዝብን መሠረታዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ገለጹ፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ካቢኔ በክልሉ ወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታ ላይ ውይይት አካሂዷል፡፡

ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁን ተከትሎ በተደራጁ አራት ኮማንድ ፖስት እየተከናወኑ የሚገኙ የሰላም ማስከበር ሥራዎችን አስመልክቶ ለካቢኔ አባላት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች ለአርሶ አደሩ በወቅቱ ሲቀርብ የነበረው የአፈር ማዳበሪያ ስርጭት በመስተጓጎሉ በመኸር ሰብል ልማት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን አንስተዋል።

ከመሃል ሀገር ወደ ክልሉ የሚገቡ ነዳጅና ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ውጤቶች፣ ሸቀጦችና የፍጆታ ምርቶች በጸጥታ ስጋት ምክንያት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይቀርቡ ጫና መፍጠሩንም ተናግረዋል፡፡

የሕዝቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት ሰላም ሲረጋገጥና ወደልማት ሥራ መመለስ ሲቻል መሆኑን ጠቅሰው፤ የክልሉን ሰላም ለማረጋገጥ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል፡፡

የክልሉን ሰላም ወደነበረበት ለመመለስ በሚደረገው ሒደትም ሁሉም ሕዝብ ከመከላከያ ሰራዊትና ከጸጥታ መዋቅር ጎን በመሆን ተሳታፊ እንዲሆን መልዕክት ማስተላለፋቸውን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመላክታል፡፡

የመንግሥት ተቋማትን በተሟላ መንገድ ወደሥራ በማስገባት በቀሪ ወራት የሚከናወኑ የትምህርት፣ የገቢና ሌሎች የልማት ሥራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ ለማከናወን ርብርብ ይደረጋልም ነው ያሉት፡፡

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር መቆየት ዘላቂ መፍትሔ አይደለም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የክልሉን ሰላም በማረጋገጥና ሕዝብ ቅር የተሰኘባቸውን ጥያቄዎችን በመለየት በቅደም ተከተል በመፍታት ክልሉን ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማውጣት እንደሚሠራም ገልጸዋል፡፡

# "አልወለድም" ያለው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመርዳት ከአፉ ያደረሰውን ኩርማን እንጀራ ትቷል:: ለወገኑ አለኝታ ሆኗል:: በአዲስ አበባና ደሴ በተከፈተው ማስተባበሪያ ጽሕፈትቤት ሰው የሚችለውን አድርጓል:: ሚሊዮኖች ፈሰስ ተደርገውበታል:: ብዙ ጉልበቶች ዝለውበታል:: የዕለት እንጀራቸውን ከሥራው ያደረጉ ለፍቶ አደሮች ድካም አለበት::

ባለሀብትና መምህራን ስፍራው ይለማ ዘንድ ይቆረቆራሉ:: አመሠራረቱም ይህ ፍላጎት የወለደው ነበር:: የደሴ ሆስፒታልን ከድካም ያሳርፋል ተብሎ ነበር:: አሁን ምን ላይና እንዴት እንዳለ መረጃ የለም፤ በደሴ ይገነባል ተብሎ የነበረው ወሎ ተርሸሪ ኬር ሆስፒታል::

ከተጀመረ ዓመታት ቢነጉዱም ዛሬም ባለበት ይረግጣል:: ታሞ መዳንን ለሻተው ሕዝብ አልደረሰም:: በመዋጮ ኪሱ የሳሳው ሀገሬው ዛሬም መዳንን ፍለጋ ብዙ ኪሎሜትሮችን ይኳትናል::

ይህ ለምን ሆነ? እንዴት ይሄን ያህል ጊዜ ፈጀ ብለን ጠየቅን:: ለጠየቅነው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የሚሰጥ አካል ግን የለም:: እስከዛሬ ምን ያህል ገንዘብ ወጣበት? ምን ያህል ሥራው ተሠርቷል? ምን ያህልስ ይቀረዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች መላሽ አካል ያስፈልጋል:: ተቋማችን በተለያዩ ጊዜያት መልስ ስጡን ሲል የሆስፒታሉን ገንቢ ደጅ አንኳኩቷል:: ምላሽ አልተገኘም እንጂ::

መልስ ቢጠፋም የደሴ ነዋሪ ምን ይላል ብለን ጠየቅን:: አስተያየት ሰጪው አቶ ሰይድ ሀሰንን አውግተናል:: ስለ ሆስፒታሉ ተቆጭተዋል:: ሆስፒታሉ ይገነባል ሲባል ስለነበራቸው ፍሰሀ አወሱን:: ደስተኛ የሆኑበትና በብዙ ተስፋ የተሞሉበት ተቋም ነበር:: ሆስፒታሉ ለማኅበረሰቡ ያለው አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው:: በአካባቢው መኖሩ በጣም ደስ አሰኝቷቸዋል:: ኮሚቴ ተቋቁሞ እንደነበር ትዝ ይላቸዋል:: እሳቸውም በገቢ ማሰባሰቢያው ላይ ተሳትፈዋል:: በግለሰብም በተቋምም ደረጃ አዋጥተዋል:: ዛሬ ግን ተስፋ ወደ መቁረጡ ነኝ ባይ ናቸው:: እንኳን ጥቅሙ መጀመሩም ናፍቆናል ይላሉ::

እሳቸው ሲያስታውሱ እንኳን በርካታ ማስታወቂያ ተሠርቶበታል:: የማኅበረሰብ ጥያቄ መሆን ችሎም ነበር:: ሕዝቡ ለግንባታው ዶሮና እንቁላሉን ሳይቀር ሸጧል:: በጊዜው የሕክምና ቱሪዝምን ያነቃቃል የሚል እምነት ተጥሎበታል:: ለነዋሪው ከሕክምና ጥያቄ በላይ ነው:: አካባቢውን ያሳድጋል:: ሕክምና ፍለጋ ወደ ውጭ የሚሄዱ ሰዎችን ቁጥር ይቀንሳል:: በሀገር ውስጥ ሕክምናን ለማግኘት ያስችላል:: የተስፋ ዳቧቸውን አርቆ ሰቅሏል:: ወይ የለ አለያም አለ እንዳይባል አድርጎ:: ሲጠብቁት የከረሙት ሆስፒታል ዛሬ የለም::

አቶ ሰይድ እገነባለሁ ያሉት ቃላቸውን ይጠብቃሉ ብለው ተስፋ ሰንቀዋል:: ካልተገነባ ሕዝብን አለማክበር ነው:: ሆስፒታሉ የማኅበረሰቡ ጥያቄና የዘወትር ናፍቆቱ ነው:: ከሕዝቡ የተሰበሰበው ገንዘብ ምን ላይ እንደዋለ መጠየቅ ያስፈልጋል:: እሳቸው አሁንም እንደ ማኅበረሰብ የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት ዝግጁ ናቸው::

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ ተከስተ ሐረገወይን ይባላሉ:: የደሴ ከተማ ነዋሪ ናቸው:: በጊዜው የነበረውን የሕዝቡን መነቃቃት የዛሬ ያህል ያስታውሱታል:: ሆስፒታሉ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ነበረው:: ሕዝቡ የእኔ የሚለውን ተቋም ለመገንባት ቁርጠኛ ነው:: በሰብስፔሻሊስት ደረጃ ታካሚን ለማገልገል ያለመ ነበር::

ቢጠናቀቅ ለወሎ ብቻ ሳይሆን ለመላው አማራ ክልል ብሎም ኢትዮጵያን መጥቀም ይችላል:: ወደ ፌዴራል ሆስፒታሎች የሚላኩ ታካሚዎችን ያክማል የሚል እምነት ነበራቸው:: ባለው አሁናዊ አቋም ግን ወሎ ሆስፒታልን እንኳን ማገዝ አልቻለም::

አቶ ተከስተ ዛሬ ላይ ስለ ሆስፒታሉ መረጃ የላቸውም:: ሥራው ግልፅነት ይጎድለዋል:: ባለቤት ሆኖ ይህን ያህል ተሰብስቧል የሚላቸው አካል አላገኙም:: ገንዘባቸውን የተወሰደባቸውን ያህል ነው የቆጥሩት:: ግንባታው ምን ያህል እንደቀረው ማንም አልተናገረም:: የነበረውን ሕዝባዊ ቅቡልነት መልሶ ለማግኘት ሥራዎች ይጠበቅበታል::

ድርጅታችን የነዋሪዎችን ቅሬታ ይዞ መልስ ፍለጋ ኳትኗል:: ምላሽ ለማግኘት በርካታ በሮችን አንኳኩቷል:: ግልፅ የሆነ መረጃ የሚሰጥ አካል የለም:: በተለይ ጉዳዩ ይመለከተዋል የተባለውን የወሎ ዩኒቨርሲቲን ጠይቋል:: ሆኖም ዛሬ ነገ እየተባለ በቂ ምላሽ ማግኘት አልተቻለም:: ካለ ምላሽ እንደምናወጣው ለዩኒቨርሲቲው ቀድመን ያሳወቅን መሆኑን መግለፅ ተገቢ ነው:: በቀጣይም ምላሽ ለሚሰጠን አካል በራችን ክፍት መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን::

# የምርት አቅርቦትና የገበያ ማዕከላትን በማስፋት የበዓል ወቅት ገበያን ማረጋጋት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት በኢትዮጵያ ፈታኝ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። ችግሩ ኅብረተሰቡን በእጅጉ እየፈተነ ሲሆን፣ ችግሩ በምርት አቅርቦት እጥረትና በሕገወጥ ነጋዴዎች እንዲሁም ደላላዎች እየተባባሰ ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ እየተባባሰ ለመጣው የኑሮ ውድነት ዓለም አቀፍ ጫናዎችም በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጥሎት ያለፈው አሉታዊ ተጽእኖ እንዲሁም በዩክሬንና ሩሲያ መካከል እየተካሄደ ያለው ጦርነት በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድረዋል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሸቀጦች ዋጋ በእጥፍ መጨመሩን መረጃዎች ያመለክታሉ። ኢትዮጵያም ከዚህ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ውጭ አይደለችም።

መንግሥት ይህ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት በሕዝቡ ላይ እያደረሰ ያለውን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ርምጃዎችን ሲወሰድ ቆይቷል፤ እየወሰደም ይገኛል። እንደ ዘይትና ስኳር ያሉትን ሸቀጦች ከውጭ ሀገር በማስመጣት ጭምር ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ ነው። በግብርና ምርቶች አቅርቦት ላይም እንዲሁ በህብረት ሥራ ማህበራትና በንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በኩል እየሰራ ነው። እንደ ስንዴ ያሉትን ሰብሎች በበጋ መስኖ ጭምር በማልማት በስንዴ ዋጋ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ማስቀረት ችሏል።

የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረቱ በተለይ በበዓላት ወቅት ጎልቶ ይስተዋላል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ይህን ችግር ለመፍታት በየበዓላቱ ወቅት አቅርቦትን በማሳደግ ገበያውን ለማረጋጋት ይሰራል። በዚህም የዋጋ ንረቱ እንዳያሸቅብና የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ ጥረት ያደርጋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከጥቂት ሳምንታት በኋላ መላው ኢትዮጵያውያን በጋራ በሚያከብሩት የዘመን መለወጫ በዓል ወቅት ይህ ችግር ሊያሳድር የሚችለውን ጫና ከወዲሁ ግምት ውስጥ በማስገባት እየሰራ ይገኛል። በዓሉን ምክንያት በማድረግ የዋጋ ማናር እና የአቅርቦት ክፍተት እንዳይከሰት ማድረግ የሚያስችሉ ተግባሮች በአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በኩል እየተሰሩ መሆናቸውን የቢሮው ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስታውቀዋል።

አሁን ያለው የኑሮ ውድነት ዓለም አቀፍ ጫና እንዳለው አቶ መስፍን ጠቅሰው፣ በተለይም በበዓላት ወቅት ተፈላጊነታቸው የሚጨምር የምርት ዓይነቶች ስለመኖራቸው ይናገራሉ። እነዚህ ምርቶች ቀድሞ ከነበረው ፍላጎት በተለየ በከፍተኛ መጠን እንደሚፈለጉና በአዲስ መልክ የሚፈለጉ የምርት ዓይነቶች ስለመኖራቸውም ገልጸው፤ ይህንኑ ፍላጎት መሠረት በማድረግም ከተማ አስተዳደሩ እየሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዋናነት መሠረታዊ የሚባሉ የሰብል ምርቶች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች፣ የተመረጡ የኢንዱስትሪ ምርቶች እና እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦዎች በበዓላት ወቅት በስፋት ይፈለጋሉ። ከዚህ አንጻር በበዓላት ወቅት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የአቅርቦት ሥራ በስፋት ይሰራል። ለዚህም አቅርቦቱን ለማሳለጥ በትኩረት ይሰራል። ምርቶቹ ወደ ከተማ በስፋት እንዲገቡ ይደረጋል። ከዚህ ባለፈም ኅብረተሰቡ ምርቶቹን በአማራጭ የገበያ ማዕከላት አግኝቶ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ ነው።

በአሁኑ ወቅትም መጪውን የአዲስ ዓመት ወይም የዘመን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድረግ የዋጋ መናርና የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ቀደም ብሎ በተጀመሩት የእሁድ ገበያዎች ላይ ምርት በስፋት እንዲቀርብ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። በመደበኛነት ካለው የእሁድ ገበያ በተጨማሪ በበዓሉ መቃረቢያ የአዘቦት ቀናትም እንዲሁ ግብይቱ የሚከናወንበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው ባዛሮችንም በሁሉም ክፍለ ከተሞች በስፋት የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል። በከተማ ደረጃም በተመረጡ አካባቢዎች ላይ ማለትም በሳርቤት፣ የካ አባዶ፣ ቃሊቲ አካባቢ አዲስ በተገነባው የገበያ ማዕከል ምርቶችን በስፋት በማቅረብ ገበያውን የማረጋጋት ሥራ ይሠራል ብለዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት ጋርም እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ የህብረት ሥራ ማህበራቱ ቀደም ሲል ምርቶቻቸውን ከሚሸጡባቸው ሱቆች በተጨማሪ በሱቆቹ አካባቢዎች ላይ አነስተኛ ድንኳኖችን በመትከል ምርቶችን በስፋት ለማቅረብ ዝግጅት ማድረጉን ነው ያመላከቱት።

«የገበያ መረጋጋቱም ሆነ የዋጋ ንረቱን የማርገቡ ሥራ በዋናነት በምርት አቅርቦት መደገፍ አለበት» የሚሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ወደ ከተማ እየገባ ካለው የምርት መጠን በተጨማሪ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ምርቶችን በስፋት ወደ ከተማዋ ማስገባት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ለዚህም በከተማ ደረጃ ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመሆን በተለይም የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን ለአብነትም የዶሮና የእንቁላል አቅርቦት ከወዲሁ በስፋት እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰዋል። ከተማ ውስጥ ከሚገኙና በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ አምራች አካባቢዎች በተለይም የዘይትና የዱቄት ምርቶች ወደ ከተማዋ እንዲገቡና በባዛሮች ላይ እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህራት የከተማ አስተዳደሩ የመደበውን ገንዘብ በመጠቀም ቀደም ብለው እያስገቡት ከነበረው ምርት በተጨማሪ በዓሉን አስመልክቶ እጥረት እንዳይከሰት የተለያዩ ምርቶችን ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጋራ በመሆን ወደ ከተማዋ የማስገባት ሥራ እየተሰራ ነው። ወደ ከተማ እንዲገቡ የተደረጉት ምርቶች በተለያዩ አማራጮች ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡና ህብረተሰቡ ምርቶቹን በአቅራቢያው ማግኘት የሚያስችል ዕድልም ተፈጥሯል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቅርቦት ላይ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግም ነው ምክትል ቢሮ ኃላፊው ያመለከቱት፤ አቅርቦት ሲሰፋ ዋጋው ላይ ለውጥ ማምጣትና ገበያውን ማረጋጋት እንደሚቻል ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አቅርቦቱም በሕገወጥ መንገድ እንዳይመዘበርና በዋጋ ንረት ችግር እንዳይፈጠር ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቷል። ለዚህም ከንግድ ቢሮ፣ ከገቢዎች ቢሮ፣ ከጸጥታ አካላት እንዲሁም ከምግብ፣ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በቅንጅት በመሆን የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ይህም በዋናነት በዓላትን ምክንያት በማድረግ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የተጋነነ ዋጋ እንዳይኖር፣ ምርትን በመከዘን ሰው ሰራሽ እጥረት እንዳይከሰት በተለይም ምርትን ከባዕድ ነገር ጋር በመቀላቀል የማኅበረሰቡን ጤና የሚጎዱ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል በተቀናጀ ቡድን በኩል ይሰራል፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግም ተገቢና ሕጋዊ ርምጃ ይወሰዳል።

የበዓል ገበያን ለማሳለጥ ከንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በመሆን በተለይም የስኳርና የዘይት ምርቶች ለበዓሉ በስፋት እየቀረቡ እንደሆነ የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ለበዓሉ ብቻ ሁለት ሚሊዮን ሊትር ዘይት እንዲሁም 36 ሺ ኩንታል ስኳር በአሁን ወቅት ወደ ከተማዋ እየገባ ስለመሆኑ ተናግረዋል። ይህ ምርት በመንግሥት ብቻ የሚቀርብ እንደሆነና ከዚህ ውጭ በመደበኛው ገበያም ተጨማሪ ምርት ይቀርባል ብለዋል። በተለይም በፍራንኮ ቫሉታ በተፈቀደው አግባብ መሠረት መጠነ ሰፊ ምርት ወደ ገበያው እየገባ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

የበዓላት ወቅቶችን ብቻ ጠብቆ በሚሰራ ሥራ የዋጋ ንረትን መከላከልና የኑሮ ውድነትን ማረገብ እንደማይቻል የገለጹት ምክትል የቢሮ ኃላፊው፤ በዋናነት ቋሚ በሆነ አግባብ መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል፤ በተለይም ከንግድ ሥርዓቱ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን ቋሚ በሆነ መንገድ መቅረፍና ማረም አስፈላጊ እንደሆነም አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ገበያውን ለማረጋጋት ዋናነት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል። ለአብነትም በከተማ ደረጃ የሌማት ትሩፋት በሚል የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፤ በተለይም በከተማ ግብርና እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችና የተለያዩ ፕሮጀክቶችንም እንዲሁ ማጠናከር ያስፈልጋል። ይህ ሥራ በከተማ ውስጥ ያለውን የምርት አቅርቦት እያሳደገ መምጣት ችሏል። በዚህም በከተማ ውስጥ ከእንቁላል ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመቅረፍ በከተማ ግብርና በተሠራው ሥራ ውጤት ማምጣት መቻሉን ምክትል የቢሮ ኃላፊው አመላክተዋል።



አቶ መስፍን አሰፋ

በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይም እንዲሁ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ ከዚህ አኳያ የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ እንደሆነ ነው ያመላከቱት።

በከተማዋ ከንግድ ሥርዓት ጋር ተያይዞ ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል ሕገ ወጥነት አንዱ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ሕገ ወጥ ንግድ የሚከናወነው በሕገ ወጥ ነጋዴዎችና በደላሎች መሆኑን ተናግረዋል፤ ይህንን ለማስቀረት በዋናነት የገበያ መሠረተ ልማቶችን ማስፋት አንዱ አማራጭና መፍትሔ መሆኑን ተናግረዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በአዲስ አበባ ከተማ አምስት የመግቢያ በሮች ላይ ትላልቅ የገበያ ማዕከላትን ለማስገንባት አቅዶ እየሠራ ስለመሆኑ የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አምራቹ ራሱ ምርቱን በእነዚሁ የገበያ ማዕከላት ማቅረብ ያስችለዋል ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪም በሕገ ወጥ ደላላ ሰንሰለት ይመጣ የነበረውን ጫና የሚያስቀርለት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ትልቅ ትርጉም ያለው ስለመሆኑ ተናግረዋል። በአሁኑ ወቅትም ገበያው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መጀመሩንና ውጤት የተመዘገበበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በበጀት ዓመቱ ግንባታቸው ከተጠናቀቁ የገበያ ማዕከላት መካከል የአቃቂ ቃሊቲ እና የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የገበያ ማእከላት ግንባታዎች ይገኙበታል። በእነዚህ የገበያ ማእከላትም ማህበረሰቡ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። የገበያ ማዕከላት መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ከተማ ውስጥ ያለውን የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሰብል ምርቶች አቅርቦት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ከማድረጋቸው በተጨማሪም በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያለውን በተለይም የሕገ ወጥ ደላላ ጣልቃ ገብነትን ማስቀረት የሚችል እንደሆነም ገልጸዋል።

በከተማ ደረጃ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት በስፋት እየተሰራ ካለው ሥራ መካከል የዳቦ ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የሸገር ዳቦን ጨምሮ በከተማ ደረጃ የግል ባለሃብቶችን በማስተባበር ዳቦ ፋብሪካዎችን በማስገንባት የተሠሩ ሥራዎች ስለመኖራቸው ተናግረዋል። እነዚህን ሥራዎች በማጠናከር በተለይም ከአቅርቦት ጋር ተያይዞ ከኅብረተሰቡ የሚነሳውን ችግር ማቃለል እንደሚቻል ነው ያስገነዘቡት። አቅርቦት ሲሰፋ ግብይቱ ላይ ውድድር እንደሚፈጠር በመጥቀስም፣ አቅራቢ አካላት ሲበዙ ውድድር እያደገ ይመጣል። በዚህም የኑሮ ውድነት ችግርን ማቃለል ይቻላል ሲሉ አስታውቀዋል።

ምክትል የቢሮ ኃላፊው እንዳብራሩት፤ ሌላው በከተማ ውስጥ የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት 18 በሚደርሱ የምገባ ማዕከላት አቅም የሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በቀን አንድ ጊዜ በነጻ መመገብ የሚችሉበት ዕድል ተፈጥሯል። የትምህርት ቤት ምገባም ሌላው የወላጆችን ጫና ለመቀነስ የተሠራ ሥራ ሲሆን፤ ከሰባት መቶ ሺ በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ እየተመገቡ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ማዕድ ማጋራት በሚል ፕሮጀክት ባለሃብቶችን በማስተባበር ሰፊ ቁጥር ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች የማገዝ ሥራ ይሠራል። እነዚህ የአጭር ጊዜ መፍትሔ የተሰጠባቸውና ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ ስለመሆናቸውም ተናግረዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እየተሠራ ነው ያሉት ምክትል የቢሮ ኃላፊው፤ በዋናነት የሚከናወነው አንዱ ተግባር ምርትና ምርታማነትን በሀገር አቀፍና በከተማ ደረጃ ማሳደግ መሆኑን ጠቁመዋል። የገበያ ማዕከላትን መሠረተ ልማት ማስፋትና ማጠናከር እንዲሁም ሕገ ወጥነትን በመከላከል ርምጃ መውሰድ ለዘላቂ መፍትሔ ወሳኝ ነው ብለዋል።

የኑሮ ውድነትን ከማረጋጋት አንጻር የእሁድ ገበያ በከተማ ደረጃ አማራጭ መፍትሔ ሆኖ አገልግሏል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አንደኛ የገበያ ተደራሽነትን ከማስፋት አንጻር ኅብረተሰቡ በአቅራቢያው ምርት ማግኘት አስችሏል ብለዋል። ሁለተኛ አማራጭ ምርቶችን ከመደበኛው ገበያ በተሻለ ዋጋ ማግኘት ማስቻሉንም ጠቅሰዋል። እንዲሁም ኅብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን ምርቶች በአንድ ቦታ በስፋት ከማግኘት አንጻርም ውጤት ተመዝግቧል ያሉት ኃላፊው፣ ከተማ ውስጥ በሁሉም ወረዳዎች ላይ ቢያንስ አንድ የእሁድ ገበያ መፍጠር ስለመቻሉ ነው የተናገሩት። ይህም በ2016 ዓ.ም ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል። በተለይም በከተማው ውስጥ የሚገኙ 172 የገበያ ማዕከላትን አንደኛ ደረጃ የገበያ ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በመጨረሻም በዓሉን አስመልክቶ ባዛሮች በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች እንደሚዘጋጁ ጠቁመው፣ በተለይም ከነሐሴ 27 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተመረጡ አካባቢዎች ባዛሩ በቋሚነት ይካሄዳል ብለዋል። የእሁድ ገበያዎችም እንዲሁ በእነዚህ ቀናት በተከታታይ እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## በማን አቆጣጠር?

**ዋስልኝ አየለ**

የዓመቱ የመጨረሻ ወር የሆነውን ነሐሴን እነሆ እያገባደድን ነው። አዲስ ዓመት ልንቀበል በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ብቻ ቀርተውናል። አዲስ ዓመት ሲገባ ደግሞ የለመድነውን የዓመተ ምህረት አጻጻፍ ትተን ሌላ አዲስ ቁጥር እንጽፋለን። እዚህ ላይ ታዲያ የብዙዎች ስህተት በለመደ አእምሮ የቆዩበትን ቁጥር መጻፍ ነው። መስከረም ወር ላይ ይህ ስህተት ያጋጥማል። ደግነቱ በዚህ ዘመን የእጅ ጽሑፍ የምንጠቀምበት አጋጣሚ እምብዛም ስለሆነ በቅጽበት ማረም ይቻላል።

በዓመተ ምህረት አጻጻፍ ውስጥ እስከ 10 ዓመት ድረስ ከአራቱ ዲጂቶች (ከ1999 ዓ.ም ወዲህ ማለት ነው) የመጨረሻዋን ዲጂት ብቻ ነው የምንቀይር። በአሥር ዓመት አንዴ ግን የ10 ቤት የሆነችዋን ዲጂት እንቀይራለን። ለምሳሌ ከ1990 ጀምሮ እስከ 2000 ድረስ የ10 ቤት የሆነችው 9 ቁጥር ለ10 ዓመታት ያህል ትቀጥላለች። ከ2001 እስከ 2009 ድረስ ደግሞ የ10 ቤት የሆነችው 0 ቀጥላለች። ከ2010 ጀምሮ ደግሞ የ10 ቤት 1 ቁጥር ናት። እስከ 2019 ድረስ ትቀጥላለች። የ100 ቤት እና የ1000 ቤት የሆኑት ግን ለመቀየር ክፍለ ዘመን (100 ዓመት) እና ሚሊኒየም (1000 ዓመት) ይቆያሉ። ከ2000 ዓ.ም በፊት የተወለደ የዚህ ትውልድ አካል ዕድለኛ ሆኖ ሚሊኒየም አክብሯል።

ወደ ዋናው ትዝብቴ ልግባ። እነሆ አዲስ ዓመት እየመጣ ነው። አዲስ ቁጥር ልንጽፍ ነው፤ 5 ቁጥር በ6 ልትቀየር ነው። በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር 2016 ዓ.ም ልንል ነው ማለት ነው።

እዚህ ላይ ታዲያ አንድ የምንታዘበው ነገር አለ። ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን...›› እያልን እንፎክራለን። የዘመን አቆጣጠራችንን የኮራንበትን ያህል ግን አንጠቀምበትም፤ የውጭው ናፋቂ ነን። በቀላሉ የጓደኞቻችሁን (የራሳችሁንም ቢሆን) ስልክ ተመልከቱ! ሰዓቱ የሚሞላው በፈረንጅኛው አቆጣጠር ነው። ቀኑ እና ዓመተ ምህረቱ የሚሞላው በፈረንጅኛው አቆጣጠር ነው። ስልኩ የኢትዮጵያን አቆጣጠር አይሰራም ይሆን?

በተለይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ ጓደኞቼ ደግሞ ከዚህም በላይ የታዘብኩት ነገር አለ። የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ይጠፋባቸዋል። ‹‹ዛሬ ቀን ስንት ነው?›› ተብለው ቢጠየቁ ‹‹ነሐሴ 24›› ከማለት ይልቅ ‹‹August 30›› የሚለው ቶሎ ትዝ ይላቸዋል። ምክንያቱም የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ከውጭው ጋር ነው የሚቀራረቡት። ደብዳቤዎችና ሌሎች የሥራ ሰነዶች የሚጻፉት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው። የወር ደመወዛቸውን የሚቀበሉት በውጭው አቆጣጠር ነው። በእነዚህ ተፅዕኖዎች ምክንያት ከኢትዮጵያው አቆጣጠር ይልቅ ለውጭው ይቀርባሉ።

የመንግሥት ተቋማት ሆነውም የውጭው አቆጣጠር ተፅዕኖ ያለባቸው አሉ። እንዲያውም ከመገናኛ ብዙኃን በስተቀር አብዛኞቹ በውጭው አቆጣጠር የሚጠቀሙ ናቸው። ለምሳሌ ባንኮች ደረሰኝ ላይ ቀን የሚጽፉት በውጭው አቆጣጠር ነው። ብዙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቀንና ዓመተ ምህረት የሚጻፈው በውጭው አቆጣጠር ነው። በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች ሁሉ በውጭው አቆጣጠር ነው። በእርግጥ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማስተማሪያ ቋንቋውም እንግሊዝኛ ስለሆነ ከተፅዕኖው ነፃ መሆን አይቻልም፤ ቢሆንም ግን ቢያንስ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚወጡና በሀገር ውስጥ ቋንቋ በሚጻፉ ማስታወቂያዎች የኢትዮጵያን መጠቀም ይቻል ነበር።

የዘመን አቆጣጠርን እያደበላለቁ መጠቀም ለመረጃ ስህተትም ይዳርጋል። አንድ በተደጋጋሚ የሚስተዋል ስህተት ላስታውሳችሁ። እንደሚታወቀው በእንግሊዝኛ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ ዓመተ ምህረት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ነው። በእንግሊዝኛ ስንጽፍም ይህንኑ ዓመተ ምህረት ነው መጠቀም ያለብን። ምናልባት የኢትዮጵያን ዓመተ ምህረት መጥቀሱ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ E.C የሚለው የተለመደ አገላለጽ አለ። ልብ ብላችሁ ከሆነ ግን ይሄን ሳይጠቀሙ በኢትዮጵያ ዓመተ ምህረት በእንግሊዘኛ የሚጽፉ አሉ። ይሄ ነገር ለስህተት ይዳርጋል።

ለምሳሌ ዓመተ ምህረቱ ያለፈ ከሆነ የሰባት ወይም የስምንት ዓመት ልዩነት ተሳስተናል ማለት ነው። ምናልባት ዓመተ ምህረቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገና ወደፊት ከሆነ ግን ከጽሑፉ ዓውድ ልንረዳው እንችላለን። ለምሳሌ ‹‹በ2018 በተደረገው...›› የሚል የሆነ ሁነት ብናነብ የኢትዮጵያ 2018 ገና ወደፊት ስለሆነ በአውሮፓውያኑ ነው ማለት ነው። ‹‹በ2010 በተደረገው... ›› ቢባል ግን የአውሮፓውያኑም የኢትዮጵያም 2010 አልፏል። ምናልባትም ጉዳዩ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ ሆኖ ከነዓመተ ምህረቱ ካላስታወስነው በስተቀር ለስህተት እንዳረጋለን።

በተመሳሳይ፤ በአማርኛ ጽሑፍ ውስጥ አቆጣጠሩ የውጭ ከሆነ እ.ኤ.አ ብሎ መግለጽ የተለመደ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን ይህን ሳይጠቀሙ በውጭው አቆጣጠር ይጽፋሉ። ይሄም ከላይ የገለጽኩትን አይነት ስህተት ያስከትላል። እንደምልከት የሚያገለግል ነገር ደግሞ አለ። ‹‹ዓ.ም›› የሚል ካለው አቆጣጠሩ በኢትዮጵያ ነው፤ ከሌለው በአውሮፓውያኑ ነው የሚባል ነገር አለ። ይሄ አከራካሪ ስለሆነ አስተማማኝ አይሆንም! የውጭውም ‹‹ዓ.ም›› ይባላል የሚሉ አሉ። ምክንያቱም በእንግሊዘኛ B.C እና A.D የሚባል ነገር ስላለ A.D ‹‹ዓ.ም›› እንደማለት ነው ብለው የሚከራከሩም አሉ፤ ለማንኛውም ይሄኛው ዘዴ የማሳሳት ዕድሉ ሰፊ ነው።

በነገራችን ላይ ጉዳዩ የሀገር ውስጥ ሆኖ የውጭውን አቆጣጠር እንዲንጠቀም የሚያስገድዱን ነገሮች አሉ። ይሄውም በራሳችን አላዋቂነት የመጣ ነው። ብዙ ነገሮቻችን በውጭዎች የተጻፉ ናቸው። ስለዚያ ጉዳይ መረጃ ፈልገን ወደ በይነ መረብ (ኢንተርኔት) ስንገባ በእንግሊዝኛ የተጻፈ ታሪክ እናገኛለን። በሀገር ውስጥ ቋንቋ ስንፈልገው ግን ዘረኝነትና የፖለቲካ ብሽሽቅ ነው የሚያመጣልን። ለምሳሌ የአንድ ታዋቂ ሰው ስም አስገብታችሁ ብትፈልጉ፤ ‹‹የእገሌ ስውር ሴራ፣ የእገሌ ገመና ሲጋለጥ...›› የሚሉ አሉቧልታዎችን ነው የሚያመጣልን። በእንግሊዝኛ ስትፈልጉ ደግሞ የሕይወት ታሪኩን፣ የሰራቸውን ሥራዎች፣ የትምህርት ደረጃውን... ይነግረናል። በእነዚህ ምክንያቶች እንግሊዝኛውን ለመጠቀም እንገደዳለን።

እንዲህ የውጭውን አቆጣጠር የመለማመዳችንን ያህል ግን ለምን ወደ ሀገርኛ መተርጎም አልቻልንም? ቀኑ እና ወሩ ከተጠቀሰ በውጭ አቆጣጠር የተጻፈን ጽሑፍ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማስቀመጥ በጣም ቀላል ነው። በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ያለን የቀን ልዩነት ይታወቃል። ያለን የዓመተ ምህረት ልዩነት ይታወቃል። ለምሳሌ ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ወራት ውስጥ የሰባት ዓመት ልዩነት ነው ያለን። በእንግሊዝኛ ጽሑፍ የተገለጸው ወር ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ከሆነ ከዓመተ ምህረቱ ላይ ሰባት መቀነስ ነው። ከጥር በኋላ የፈረንጆች ዓመት ስለሚታደስ ከጥር እስከ ነሐሴ ባሉት ወራት ደግሞ ልዩነታችን ስምንት ስለሆነ ስምንት መቀነስ ነው። ቀኑም ልክ እንደዚሁ! ለምሳሌ አሁን በነሐሴ ወር ያለው ልዩነት ስድስት ሲሆን በመስከረም ወር ደግሞ 10 ነው።

ይሄኛው አቆጣጠር ውሰብሰብ ስለሚል ሁሉም ይጠቀመው ማለት አይቻልም፤ ቢያንስ በምርምር ላይ ያሉ ሰዎች ግን እንዴት ይሄ ይጠፋቸዋል? እሺ ይሄም ይቅር! ሀገራዊ ሁነትን በራስ አቆጣጠር ቢጻፍ ምን ችግር አለው? ምናልባት መሰልጠን እየመሰለን ነው አይደል? ሰው እንዴት የራሱ አኩሪ ታሪክ እያለው የሌላው ይናፍቀዋል?

እዚህ ላይ ግን አንድ ትልቅ ኢትዮጵያዊ ምሁር ማመስገን እፈልጋለሁ። የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በቅርቡ የሕይወት ታሪካቸውን ጽፈው ነበር። የእርሳቸው የሕይወት ታሪክ የኢትዮጵያና የዓለም ታሪክ ማለት ነው። እኚህ ምሁር በመጽሐፋቸው ምረቃ ላይ ሲናገሩ እንደሰማሁት፤ ዓለም አቀፍ ሰነዶችን አገላብጠው መጽሐፉን ሲጽፉ ሰፊ ጊዜ የወሰደባቸው ዓመተ ምህረቶችን ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር መመለስ ነበር። የሀገሬን ሁነት በውጭ አቆጣጠር አልጽፍም ብለው ነው ይህን ያደረጉት። ይህ የኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች ሁሉ ልምድ ይሁን!

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ የአየር ክልሏ በአሜሪካ መጣሱን ተከትሎ ተዋጊ ጀቶችን አሰማርታ እንደነበር ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ ከትናንትና በስቲያ በጥቁር ባህር በኩል ያለው ድንበሯ በአሜሪካ ድሮኖች መጣሱን ተከትሎ ተዋጊ ጀቶችን አሰማርታ እንደነበር የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገልጿል።

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ በቴሌግራም ገጹ ባወጣው መግለጫ ድሮኖቹ ክሪሚያ አቅራቢያ ታይተው እንደነበር እና ለስለላ አላማ ወደ ሩሲያ ድንበር እያመሩ ነበር ብሏል። ሚኒስቴሩ እንደገለጸው የሩሲያ የጸረ- ኤርክራፍት ኃይል የአሜሪካ የስለላ ድሮኖችን በማስጠንቀቅ አቅጣጫቸውን እንዲቀይሩ ተደርጓል ብለዋል። ሮይተርስ የዚህን ጉዳይ ትክክለኛነት ማጣራት እንደማይችል ገልጿል።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ ልዩ ያለችውን ወታደራዊ ዘመቻ ማወጇን ተከትሎ አሜሪካን ጨምሮ ምዕራባውያን ሀገራት ከሩሲያ ጋር ያላቸው ግንኙነት ችግር ውስጥ ገብቷል። ምዕራባውያን ሀገራት በሩሲያ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ ማዕቀቦችንም ጥለዋል።

ምዕራባውያን ከማዕቀብ ባለፈም ዩክሬን ሩሲያን እንድትመክት በሚል ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ድጋፍ ማድረጋቸውን ቀጥለውበታል። ሩሲያ ለምዕራባውያን ጫና ሽብረክ እንደማትል በተደጋጋሚ ገልጻለች።



## የሱዳን ጦር መሪ አልቡርሃን ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ውጭ አቀኑ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሱዳን ጦር መሪ እና የሱዳን የሽግግር ሉዓላዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አልቡርሃን የመጀመሪያ በሚሆነው ጉብኝታቸው ወደ ግብጽ አቅንተዋል።

ምክር ቤቱ ባወጣው መግለጫ አልቡርሃን በግብጹ ከፕሬዚዳንት አልሲሲ ጋር እንደሚገናኙ ገልጿል። ምክር ቤቱ እንደገለጸው በዛሬው እለት ወደ ግብጽ ያቀኑት የሱዳን ጦር መሪ ጄኔራል አልቡርሃን በግብጿ ኢል አላሚን ከተማ ከፕሬዚዳንት አልሲሲ ጋር ተገናኝተው ይወያያሉ።

በሱዳን፣ በሱዳን ጦር እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች መካከል ጦርነት ከተቀሰቀሰበት ባለፈው ሚያዝያ ወር ወዲህ አልቡርሃን ወደ ውጭ ሲወጡ ይህ የመጀመሪያቸው ነው። አልቡርሃን ካሃዲ ያሏቸው ኃይሎች መሸነፍ እንዳለባቸው እና ከእዚህ ጋር መነጋገር አስቸጋሪ እንደሆነም ገልጸዋል።

አልቡርሃን ይህን ያሉት የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች በዘላቂነት ተኩስ ለማቆም እና በሱዳን የወደፊት እጣ ፋንታ ላይ ለመነጋገር ዝግጁነቱን መግለጹን ተከትሎ ነው። በጦርነቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን ሀገራቸውን ጥለው ሲሰደዱ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ደግሞ ከቀያቸው ተፈናቅለዋል።

# ብሪክስ- ሌላኛው የኢኮኖሚና የንግድ ልውውጥ አማራጭ

ሰው መሆን

የዓለም መንግሥታት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግብ በማስቀመጥ ብሔራዊ ጥቅማቸውን በሚያስጠብቅ መልኩ በርእዮተ ዓለም ከሚመስሏቸው አጋሮቻቸው ጋር ይሰባሰባሉ። ከዚህ መሰል ስብስብ ውስጥ ደግሞ በኢኮኖሚ፣ በቴክኖሎጂና በወታደራዊ አቅማቸው በፈረጠሙ አራት ሀገራት (ራሺያ፣ ብራዚል፣ ሕንድ እና ቻይና) ይሁንታ የተመሰረተው፤ በኋላም ደቡብ አፍሪካን ያካተተው የ"ብሪክስ" ቡድን ይገኝበታል።

ይህ ስብስብ በሀገራቱ መካከል የሚደረግ የንግድ ልውውጥ፣ እየተቀየረ የመጣውን ጂኦ-ፖለቲካዊ አሰላለፍ ቅርፅ የሚወስን እንዲሁም በምዕራባዊያኑ ተፅእኖ ስር የሚገኘውን የዓለም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ተፅዕኖ የሚቋቋምና የሚገዳደር ጭምር እንደሆነ ይታመናል።

የዓለምን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቅርፅ ከመወሰን ባለፈ የመቆጣጠርና የመምራት አቅምን የሚፈጥር ይህን መሰል ስብስብ ውስጥ መሳተፍ ደግሞ የሁሉም ሀገራት ፍላጎትና ምኞት ነው። ለዚህም ነው የምድራችንን 40 በመቶ የሚሆነውን የሕዝብ ቁጥር እንዲሁም 26 በመቶ የኢኮኖሚ ድርሻ በቅንጅት የያዙት አምስት ሀገራት "ብሪክስ" የሚል ስያሜ ያለው ቡድን የመሰረቱት።

ሀገራቱ በዚህ ሳይገደቡ አድማሳቸውን እያሰፉና አዳዲስ አባላትን እያካተቱ የዓለምን የኃይል አሰላለፍ ለመቀየር እየተንቀሳቀሱ ነው።

ኅብረቱ የወጪ ገቢ ምርቶችን ገበያ አማራጭን፣ የፋይናንስ የብድር ምንጭን ለማስፋት፣ በጥቂት ሀገራት በሚዘወርና ርእዮተ ዓለምና ፖሊሲ ተፅዕኖ ውስጥ ላለመውደቅ እንዲሁም ከቅድመ ሁኔታ ጋር የሚመጣ የድጋፍ ተፅዕኖ ውስጥ ላለመውደቅ ሰፊ እድል ይዞ እንደሚመጣ ይታመናል። ለዚህም ነው ባሳለፍነው ሳምንት ኢትዮጲያ እነዚህን እድሎች የሚከፍትላት "የብሪክስ" አባልነት ይሁንታን ስታገኝ ብዙ ያነጋገረው።

ከዓለም የንግድና የፖለቲካ ሥርዓት የአንበሳውን ድርሻ ለመያዝና ተፅእኖ ፈጣሪ ሆኖ በቀዳሚነት ለመሳተፍ ቀላል የማይባል ፍትጊያ መደረጉ የማይቀር ነው። በገቢና ወጪ ምርት ዳጎስ ያለ ሀብትን የሚያጋብሱ ኃያላን ሀገራት በንግድ ሂደቱ የሚኖራቸው ሚና ድንበር የተሻገረ፣ ሀገራትን፣ አህጉርን ያቆራረጠ የጂኦ-ፖለቲካ አድማሱን ያሰፋ ነው። በዚህ ድምፅ አልባ ሽኩቻ ውስጥ የራስን ድርሻ ማንሳት ተገቢና ፍትሐዊ ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየ ፍላጎት እንደሌላት ግልፅ ነው።

ብሪክስ "አፍሪካ አውት ሪች" እና "ብሪክስ ፕላስ" የሚል ስያሜ የሰጠውን ስብሰባ የደቡብ አፍሪካ የንግድ መዲና በሆነችው ጆሀንስበርግ ባካሄደበት ወቅት ኢትዮጲያን በአባል ሀገርነት መቀበሉን አብስሮናል። ከኢራን፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ ግብፅ፣ አርጀንቲና እና ሳውዲ አረቢያ ጋር ከሚቀጥለው ዓመት ጥር ወር ጀምሮ በሙሉ አባልነት በመቀበል የምትሳተፈው ኢትዮጵያም በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ ጥቅምን ከማስጠበቅ አኳያ ታላቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ማስመዝገብ ችላለች።

የብሪክስ ጥምረት አባል የሆነችው ኢትዮጵያ የአባልነት ይሁንታ ማግኘቷ ምን አንድምታ ይኖረው ይሆን? ምንስ አይነት እድሎች ይዞ ይመጣል? ይህንን ለመገንዘብ የሀገራቱን የኢኮኖሚ ተፅዕኖ በቁጥር አስደግፌን ከዚህ እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክር።

**በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2021 የወጣ መረጃ እንደሚያመለክተው የብሪክስ ሀገራት በጋራ 3 ነጥብ 24 ቢሊዮን ሕዝብ ብዛት ነበራቸው ( ይህ ቁጥር እየጨመረ እንደሚመጣ ልብ ይሏል።) አሀዙን በመቶኛ ስናስቀምጠው ከዓለም ሕዝብ ከ40 በመቶ በላይ እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ የምንገነዘበው ከፍተኛ አምራችና ሸማች ኃይል በብሪክስ ሀገራት ውስጥ መኖሩን ነው። ይህ የሕዝብ ቁጥር ኢትዮጵያ በግብርናና በመሰል ምርቶች በኢምፖርት ኤክስፖርት ዘርፉ ላይ ትልቅ እድል ይዞ የሚመጣ ይሆናል**

በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2021 የወጣ መረጃ እንደሚያመለክተው የብሪክስ ሀገራት በጋራ 3 ነጥብ 24 ቢሊዮን ሕዝብ ብዛት ነበራቸው ( ይህ ቁጥር እየጨመረ እንደሚመጣ ልብ ይሏል።) አሀዙን በመቶኛ ስናስቀምጠው ከዓለም ሕዝብ ከ40 በመቶ በላይ እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ የምንገነዘበው ከፍተኛ አምራችና ሸማች ኃይል በብሪክስ ሀገራት ውስጥ መኖሩን ነው። ይህ የሕዝብ ቁጥር ኢትዮጵያ በግብርናና በመሰል ምርቶች በኢምፖርት ኤክስፖርት ዘርፉ ላይ ትልቅ እድል ይዞ የሚመጣ ይሆናል።

አሁንም ከሁለት ዓመት በፊት ያለውን የሀገራቱን ጥቅል ኢኮኖሚ አቅም ስንመለከት የብሪክስ አባል ሀገራት በዓለማችን ላይ ግንባር ቀደም የኢኮኖሚ ባለቤት መሆናቸውን እንገነዘባለን። በሀገር ውስጥ ምርት ጥቅል መረጃ መሰረት ሀገራቱ በጥምረት ከ26 ነጥብ 03 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የሚለካ ምርት አላቸው። ይህም ከዩናይትድ ስቴትስ አጠቃላይ ምርት ብልጫ ያለው ነው። በዚህ ስብስብ ውስጥ መካተት እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን በሚያስጠብቅ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሳተፍ ከብሔራዊ ጥቅም አንፃር ፋይዳው ጉልህ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

ከአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ከ2000 ጀምሮ ቻይና ከብሪክስ ሀገራት ቀዳሚዋና ትልቋ የሸቀጦች ላኪ ነች። አሁንም ድረስ ከኅብረቱ የወጪ ንግድ ድርሻዋ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። የቻይና ኤክስፖርት ድርሻ በ2000 ከ50 በመቶ በላይ የነበረ ሲሆን፤ በ2020 ይህ ድርሻ ወደ 74 በመቶ ከፍ ብሎ ነበር። ሩሲያ ደግሞ ወደ ውጪ በምትልካቸው ምርቶች ሁለተኛ ደረጃ ትቀመጣለች።

ይህ እውነታ ኢትዮጵያና በኅብረቱ ይሁንታን ያገኙት አዳዲስ አባላት በዓለም የንግድ ልውውጥ ውስጥ የመደራደር አቅማቸውን ተጠቅመው የገቢ ንግድ አድማሳቸውን ማስፋት የሚያስችላቸው ታላቅ ስብስብ ውስጥ መሆናቸውን የሚያስገነዝበን ነው። ጉዳዩን በዝርዝር ለማጤን እንዲያስችለን የንግድ ልውውጡን ሀገራቱ ካላቸው የመግዛት ፍላጎትና አቅም አንፃር እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክር።

የብሪክስ አባል ሀገራት በዓለም ላይ ያሉ ሸቀጦችን ወደ ሀገራቸው በማስገባት እረገድ 14 በመቶ ጥቅል ድርሻ እንዳላቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። የቻይናን የገቢ ንግድ ብቻ ነጥለን ስንመለከት እስከ ሁለት ትሪሊዮን ዶላር ሲደርስ በጥቅሉ አምስቱ ሀገራት ደግሞ 3 ነጥብ 6 ትሪሊዮን ዶላር የገቢ ንግድ ልውውጥ እንዳላቸው ቁጥሮች ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸውን ምርቶች መጠን ማሳደግ ከቻለችና የብሪክስ አባልነት አጋጣሚውን ለዲፕሎማሲያዊ የድርድር መድረክ በተገቢው መንገድ ከተጠቀመችበት በንግድ ትስስሩ (በኤክስፖርት ዘርፉ) ግዙፍ እመርታን እንደምታሳይ ነው። በተለይ ምርቶችን ከቀረጥ ነፃ በሆነ መድረክ ለገበያ እንድታቀርብ መሰል እድሎች የሚከፍቱት በር ቀላል አንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

የብሪክስ ቡድን አባል ሀገራትን ኅብረት መቀላቀል ከላይ ካነሳነው ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ የዘለለ ፋይዳም አለው። በተለይ የእጅ መንሻን ከፊት ለፊት አድርጎ ከጀርባ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ድብቅ ሴራና አላማን ለማስፈፀም ፍላጎት ያላቸው ምእራባውያንን ቆም ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው። ይህንን ጉዳይ ዘርዘር ባለ መልኩ ወደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ መልሰነው ለመመልከት እንሞክር።

ምእራባውያን በፋይናንስ ተቋማቶቻቸው፣ በእርዳታ ድርጅቶች እንዲሁም (በጂ 7፣ በዓለም ባንክ በአውሮፓ ኅብረት...) በልዩ ልዩ ስብስቦቻቸው አማካኝነት ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማስፈፀም ይፈልጋሉ። ለፕሮጀክቶች ግንባታ ብድር አሊያም እርዳታን ሲሰጡ ከጀርባ የባህል ተፅዕኖ፣ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት፣ ሊበራላይዜሽን፣ የፋይናንስ ተቋማት ጣልቃ ገብነት፣ መንግሥት የመሾምና የመሻር አጀንዳን አግተልትለው ይመጣሉ።

በተለይ ከባህልና ከወግ ጋር ፍፁም ተቃራኒ የሆኑ አፈንጋጭ ልምዶችን ለማስረፅ የኢኮኖሚ ጡንቻቸውንና ማእቀባቸውን እንደ መሳሪያ ይጠቀሙበታል። ይህንን በማር የተለወሰ መርዝ በጣጥሶ ማለፍ የሚቻለው ከእነርሱ በተቃራኒው ከቆመ ስብስብ አሊያም አማራጭ ጋር ራስን በማወዳጀት መሆን አለበት (እንቁላልህን በአንድ ቅርጫት ውስጥ አታስቀምጥ ይሉትን ይትብሃል ልብ ይሏል)።

ከበላያችን ያነሳነውን ጉዳይ የሚያስረዱልን ሁለት የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎች ለማንሳት ስንሞክር "የዓለም ባንክ፣ አጎአ" ጋር ያደርሰናል። ከሰሞኑ ኡጋንዳ የተመሳሳይ ፆታ (አፀያፊ ተግባርን) በሕግ በመከልከሏ የተነሳ በዓለም ባንክ ምንም አይነት እርዳታና ብድር እንዳታገኝ መታገዷን ሰምተናል። ምእራባዊያኑ "የአንድ ዓለም ሥርዓት" በመዘርጋት በመረባቸው ውስጥ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ለመክተት እንደሚሞክሩ አንዱ ምሳሌ የኡጋንዳ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ቁልጭ ባለ ምሳሌ ያሳየናል።

ሌላው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ኢትዮጵያ በገጠማት የውስጥ ችግር ምክንያት አሜሪካ እንድንከተለው የፈለገችውን ፖሊሲ ባለመቀበላችን ምክንያት እንደ ዳረጎት የሰፈረችልን ከቀረጥ ነፃ ሸቀጦችን ወደ ሀገሯ የማስገባት (አጎአ) እድል መሰረዟ ነው። ይህ ዓይነት ስልት የአሜሪካ፣ አውሮፓ፣ የዓለም ባንክ እና መሰል ስብስብ ታዳጊ ሀገራትን በተፅዕኖ ስር ለመጣል የሚከተሉት ፖሊሲ ነው።

በመሆኑም በራስ አቅም ምርትን በመሸፈን፣ ቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ ላይ በማተኮር ከሚደረግ ቀጥተኛ ትግል ባሻገር የእነዚህን ኃያላን ብርቱ የማሽመድመድ አቅም ሊያዳክም የሚችል ስብስብና ኅብረት ውስጥ ያለማቅማማት መሳተፍ ተገቢ ነው። ይህ አካሄድ ብዙ አማራጭ በጠረጴዛው ላይ እንድናገኝ ያስችለናል። ከሰሞኑ የሰማነው የብሪክስ አባል ሀገራት ዓለም አቀፍ ተፅእኖና ቡድኑን ለመቀላቀል ፍላጎት ያላቸው ሀገራት እየጨመረ መሄድ አንድምታም ከዚህ መሰል ተፅዕኖ የመላቀቅ ጉጉትን የሚያመላክት ነው። ኢትዮጵያም ሳይረፍድ ከአምስቱ አባል ሀገራት ጋር መቀላቀሏ ይህንኑ ያሳያል።

በጥቅሉ የዓለም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቅርፅ ከአንድ ወገን የበላይነት እየተላቀቀ በፍጥነት ቅርፁን እየቀየረ የመምጣቱ ጉዳይ እውነታ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ሂደቱ በማደግ ላይ የሚገኙ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ቀላል አንድምታ አይኖረውም። የፖሊሲ ጫናና በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ብድርና ድጋፍ የሚታወቁት ምእራባውያን በተለይ አፍሪካ ላይ የሚኖራቸው ፖሊሲ በድጋሚ እንዲያጤኑት የሚያስገድድም ነው። ኢትዮጵያ ለምትከተለው ባለብዙ መድረክ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትም እንደ ተጨማሪ አማራጭ ልናየው የሚገባም ነው። ሰላም!

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወልደማርያም
## (ከ1921-2015 ዓ.ም)

ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ ለሕትመት ብርሃን የበቃው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚታተመው ዘኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ አማርኛ ለማይችሉ ውጭ ሀገር ሰዎች የኢትዮጵያን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በማስተዋወቅ ረገድ የማይተካ ሚና ተጫውቷል።

ከአዲስ ዘመን ቀጥሎ በአንጋፋነቱ የሚጠቀሰው ዘኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ የኢትዮጵያን ታሪክ በእንግሊዝኛ እየሰነደ ዛሬ ላይ ደርሷል። ጋዜጣው በየዘመናቱ የነበሩት ውጣ ውረዶች ሳይበግሩት የየዕለቱን ክስተት እየዘገበ እና የኢትዮጵያን ታሪክ እየመዘገበ 80 ዓመታትን ደፍኗል።

ጋዜጣው ሲመሰረት በሀገር ውስጥ በቂ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት የለም በሚል ዕሳቤ በዋና አዘጋጅነት ተመድበው ሲሰሩ የነበሩት የውጭ ሀገር ዜጎች ናቸው። ሆኖም አንድ ኢትዮጵያዊ ይህንን ሂደት ሰብሮ የመጀመሪያው የኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ለመሆን በቅቷል። ይህ ሰው ያዕቆብ ወልደማርያም ይባላል።

አንጋፋው ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወልደማርያም ከእናታቸው ወ/ሮ ወለተሚካኤል ሰንበቶ እና ከአባታቸው አቶ ወልደማርያም ሹባ በቀድሞው ወለጋ ክፍለ ሀገር ነቀምቴ ከተማ ሰኔ 12 ቀን 1921 ዓ.ም ተወለዱ።

እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ፣ በነቀምቴ ከተማ የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ማለትም ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የስምንተኛ ክፍል ፈተና ውጤታቸው ከፍተኛ በመሆኑ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተዋል።

በጊዜው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ይከታተሉባቸው ከነበሩት ተፈሪ መኮንን ትቤት፣ ጄኔራል ዊንጌት ት/ቤት እና ኮተቤ ት/ቤቶች መካከል ጋዜጠኛ ያዕቆብ በኮተቤ ትምህርት ቤት ተደልድለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። በጊዜው ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች የወቅቱን የለንደን ማትሪኩሌሽን ፈተና በከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ተማሪዎች የውጭ ሀገር ትምህርት ዕድል ይሰጥ ነበር። ከላይ ከተጠቀሱት ት/ቤቶች ከእያንዳንዳቸው ለሶስት ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ሲሰጥ፣ አቶ ያዕቆብም ከዘጠኙ አንዱ ሆነው ወደ እንግሊዝ ሀገር እኤአ በ1950 ዓ.ም ማምራት ችለዋል።

በዚያም በKingston upon-Thames Technical College የዩኒቨርሲቲ ኦፍ ለንደን ተማሪ ሆነው የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ተከታትለዋል።

እንግሊዝ ሀገር በነበሩበት ጊዜ ወ/ሮ ሲሊቪያ ፓንክረስት ታዘጋጀው በነበረው "ኒው ታይምስ" እና "ኢትዮጵያን ኒውስ" በሚባለ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ላይ ጽሑፎችን በመጻፍ ያሳትሙም ነበር። የጋዜጠኝነት ሙያ ወደ ውስጣቸው ዘልቆ የገባው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረገው ደግሞ የማኡ ማኡ የነፃነት ትግል በኬንያ ሲካሄድ እዚያው ኬንያ ሆነው ሁኔታውን መታዘባቸው ነበር። ነጮቹ በሚጽፏቸው አርቲክሎች አፍሪካውያንን ሰብዕና ላይ ጭራና ቀንድ እየቀጠሉ እንዴት አድረገው ከሰውነት በታች (ዲ-ሂውማናይዝ) እንደሚያደርጉ አንብበዋል። በዚህም የተነሳ በእንግሊዝኛ መጻፍና ትክክለኛውን የአፍሪካውያን ሥዕል መስጠት የግድ መሆኑን አምነው በስፋት፣ ሰርተዋል።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወደ ሀገራቸው በመመለስ በእጅጉ የሚወዷትን ኢትዮጵያን በተለያዩ ሙያዎች አገልግለዋል።

**በዋናነት የሚጠቀሱትም**

1. በወለጋ ክፍለ ሀገር ነቀምቴ ከተማ ለአንድ ዓመት በመምህርነት፤
2. በቀድሞ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ለአንድ ዓመት፤
3. በውሃ ክፍል ለአንድ ዓመት፤
4. በአምሃ ደስታ ት/ቤት ለአንድ ዓመት በመምህርነት ያገለገሉ ሲሆን፤ ፤



ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወልደማርያም

ከእነዚህ ዓመታት አገልግሎት በኋላ ጓደኞቻቸው ለጋዜጠኝነት የነበራቸውን ዝንባሌና ከፍተኛ የሆነውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶቻቸውን በመገንዘብ በቀድሞው ጽሕፈት ሚኒስቴር ስር በነበረው ዘ ኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ እንዲቀጠሩ ይመክሯቸዋል።

እሳቸውም በጊዜው ዋና አዘጋጅ ወደነበረው አሜሪካዊው ዴቪድ ታልቦት ጋር ሄደው ይህንኑ ጥያቄ አቀረቡለት። ታልቦትም አንድ ጽሑፍ እንዲጽፉ ይጠይቃቸዋል። እዚያው ተቀምጠው ሃሳባቸውን አደራጅተው ጽፈው ይሰጡታል። ይበልጥ የቋንቋ ችሎታቸውን ለመገንዘብ በፈረንሳይኛ የተጻፈ ሌላ ጽሑፍም እንዲተረጉሙ አዘዛቸው፣ ይህንንም በቅልጥፍናና በብቃት ተገበሩ። በአጻጻፍ ክህሎታቸው የተደነቀው ታልቦት ወዲያውኑ ወደ ሚኒስትሩ ወስዶ በማግባባት እንዲቀጠሩ አድርጓል።

የዘኢትዮጵያን ሔራልድ የቀድሞ ዋና አዘጋጆች ቋንቋውን የሚያውቁ የውጭ ሀገር ዜጎች ነበሩ። ጋዜጠኛ ያዕቆብ ባስመዘገቡት ከፍተኛ የሥራ ውጤትና ድንቅ አጻጻፋቸው የተነሳ በጋዜጣው ላይ ከተቀጠሩ ከሁለት ዓመት በኋላ በ1959 ዓ.ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የዘኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኑ።

በጋዜጣው ላይ በሰሩባቸው ዓመታት በርካታ የኤዲቶሪያል ውሳኔዎችንና ጽሑፎችን አበርክተዋል። በተለይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ መሥሪያ ቤት እንዲቋቋምና ዘመናዊ የሰው ኃይል አደረጃጀት በሀገሪቱ እንዲኖር በርካታ ጽሑፎችን ጽፈዋል። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ንግግሮችም በግሩም እንግሊዝኛ እየተረጎሙ ለውጪው ማኅበረሰብ መልዕክቱ እንዲደርስ ያደርጉ ነበር።

በጊዜው አፄ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን ለማዘመን ይተጉ እንደነበር ጋዜጠኛ ያዕቆብ በሕይወት እያሉ ከዘ ኢትዮጵያን ሔራልድ ጋር እኤአ በኦክቶበር 12 ቀን 2021 ባደረጉት ቃለ ምልልስ ተናግረዋል። ሆኖም ግን ጋዜጠኛ ያዕቆብ የመሬት ይዞታው ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለድህነት አጋልጦታል የሚል አቋም ስለነበራቸው ይሄው እንዲስተካከል ግፊት ያደርጉ ነበር።

ሌላው በተለይ የንጉሡ ሹመኞች በሕዝብ ላይ በደል እያደረሱ ነው የሚል ይዘት ያለው የሰላ ትችትም ያቀርቡ ነበር። ከዚህ ውስጥ ተጠቃሽ ጽሑፋቸው "rotten at the root" የሚል ኤዲቶሪያል ነው። በጸረ ኮሎኒያሊዝምና ጸረ ኒዮኮሎኒያሊዝም አቋማቸውም ይታወቃሉ። በአዲስ አበባ ካሉ ኤምባሲዎችም በዚህ ከፍተኛ ነቀፌታ ይደርስባቸው እንደነበር ተናግረዋል። እንዲህ ያሉ ጽሑፎችን እንዲያቆሙ ማሳሰቢያ እንደደረሳቸውና እሳቸውም በምላሻቸው ሊቆም የሚችለው እነሱም እኩይ ተግባራቸውንና አስተሳሰባቸውን ሲተው እንደሆነ በወቅቱ ተናግረዋል።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ የጋዜጠኝነት ሙያቸው በሚፈቅደው ልክ ለእውነት ቆመው ተከራክረዋል። ሕዝቡ በሹመኞች እንዳይበዘበዝና ጋዜጣውም የሹመኞች ድምጽ ብቻ እንዳይሆን በብዙ ደክመዋል። ሕዝቡን የሚያማርሩ አሰራሮችን በመገሰጽ እንዲስተካከሉ አድርገዋል። ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ የዘመኑ ሹማምንትን ገስጸዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ በውጭው ዓለም ዘንድ መልካም ገጽታ እንዲኖራት ያለመታከት ጽፈዋል። ኢትዮጵያ ተስማሚ አየር ንብረትና ለእርሻ ምቹ መልክዓ ምድር እንዳላት በኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ ላይ ለዓመታት ጽፈዋል።

በተለይም ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሉዓላዊነት የማያስደፍሩ፤ በሀገራቸው የመጣባቸውን ጠላት በአንድነት መክተው የሚመልሱ የአፍሪካውያን የነጻነት ተምሳሌት መሆናቸውን የሚያሳዩ ጽሑፎችን ጽፈዋል። የዓድዋን ተጋድሎና ቀጥሎ የመጣውን የጣሊያኑን የአምስት ዓመታት ወረራ ለውጭ አንባቢያን አስገንዝበዋል። በዚሁም የቅኝ ግዛትን አስከፊነት በብዕራቸው ገልጸው ለውጭ አንባቢያን መልዕክት አስተላልፈዋል።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ ምንም እንኳ በርካታ ዓመታት በመንግሥትና የሕዝብ ጋዜጣ ላይ ቢሰሩም፣ ለሃሳብ ብዝሃነት ያላቸው ጽኑ አቋም በሥራዎቻቸው ላይ ይታያል። ሕዝቡና መንግሥት ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙም ይሰሩ እንደነበር ሥራቸው ይገልጣል። ለምሳሌ ያልተሳካውን የነዋይ ወንድማማቾች የመንግሥት ግልበጣን (የታኅሳሱ ግርግር)ን በተመለከተ፣ አንዱ ሌላውን ለመወንጀልና በንጉሡ ፊት ለማሳጣት ይሞክር እንደነበረ ጋዜጠኛ ያዕቆብ ለዘኢትዮጵያን ሔራልድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ አመላክተዋል። ይህንን ተከትሎም lack of information is a fundamental problem of the country' የሚል ጠንካራ ኤዲቶሪያል ጽፈዋል።

የራሺያን የየካቲትና ጥቅምት አብዮቶች አድንቀውም በስማቸው ጽሑፎችን ያትሙ ነበር። ምናልባትም ይህ ጽሑፍና ሌሎች የኤዲቶሪያል አቋሞቻቸው በዋና አዘጋጅነት ሥራቸው እንዳይቆዩ አድርጓቸዋል።

አንዳንዶች የጋዜጠኛ ያዕቆብ እንግሊዝኛ ጠጣር እንደሚል ይናገራሉ። እርሳቸውም ይህንን ሆነኝ ብለው እንደሚያደርጉትና ተራ ካድሬ በቀላሉ እንዳይገነዘብና እንዳያስቆማቸው እንደሆነ የተናገሩበት አጋጣሚ አለ።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ በአጠቃላይ በአሁኑ አጠራር የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቀድሞ አጠራሩ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስር በነበረው ፕሬስ መምሪያ ለ37 ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን፤ ከዘኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ በተጨማሪ በቮይስ ኦቭ ኢትዮጵያ፣ በመነን፣ በየካቲት ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ሰርተዋል።

ከመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት ውጭም በተለያዩ በእንግሊዝኛ በሚታተሙ የግል ጋዜጦች ላይም ሰርተዋል። ከእነዚህም መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት፤ በእንግሊዝኛ የሚታተመው አዲስ ትሪቢዩን ጋዜጣ ላይ ለስምንት ዓመታት፣ በእንግሊዝኛው ዘ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ለ20 ዓመታት በዋና አዘጋጅነት ጭምር አገልግለዋል።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ ከመስከረም 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመዘዋወር፤ በሚኒስቴሩ ይታይ የነበረውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ክፍተት ለመሙላት በፕሬስና ኢንፎርሜሽን ክፍል ለ7 ዓመታት ሀገራቸውን አገልግለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት 50ኛ የምስረታ በዓሉን ሲያከብር ጋዜጠኛ ያዕቆብ ኒውዮርክ ሄደው ታድመዋል። አርቲክልም ጽፈው አሳትመዋል።

በ2007 ዓ.ም በሚዲያና ጋዜጠኝነት ዘርፍ የዓመቱ በጎ ሰው ሽልማት አሸናፊም ነበሩ።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወልደማርያም ሹባ በሕይወት ሳሉ 10 ልጆች ሲያፈሩ፣ በሕይወት ካሉት 4 ወንድና 3 ሴቶች ልጆቻቸው ስምንት የልጅ ልጅ እንዲሁም አንድ የልጅ ልጅ ልጅ አይተዋል።

ጋዜጠኛ ያዕቆብ ወልደማርያም ባደረባቸው ህመም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በ94 ዓመታቸው ነሐሴ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት ነሐሴ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ረቡዕ አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የዓለም ቻምፒዮናው ውጤት ለኦሊምፒክ የሚያተጋ የቤት ሥራ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

በ19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከተሳተፉት ሀገራት መካከል የሜዳሊያ ሰንጠረዡ ውስጥ መግባት የቻሉት 46 ብቻ ናቸው። የውድድሩ ድምቀትና የሜዳሊያ ተፎካካሪ የሆነችው ኢትዮጵያም ባስመዘገበቻቸው 9 ሜዳሊያዎች አማካኝነት ከቀዳሚዎቹ ተርታ ልትሰለፍ ችላለች። ከ5 በላይ ሜዳሊያዎችን ካስመዘገቡ 6 ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ በወርቅ ሜዳሊያዎች በመበለጧ ከዓለም 6ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 2ኛ ደረጃን በመያዝ ቻምፒዮናውን አጠናቃለች።

ለዘጠኝ ቀናት በተካሄደው ቻምፒዮና ወራት ብቻ ለሚቀሩት የፓሪሱ ኦሊምፒክ የቤት ሥራ የሰጠ እንዲሁም ቡድኑ ያለበትን ችግር በግልጽ ያመላከተ ሆኖም ነው የተደመደመው። በአስቸጋሪና ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታ ውስጥ አልፎ የዚህ ውጤት ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን ትናንት ማለዳ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል። በመካከለኛና ረጅም ርቀቶች በ34 አትሌቶች የተሳተፈው ልኡኩ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ሲደርስ በከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች የአበባ ጉንጉን ተበርክቶላቸዋል።


ፎቶ- እዮብ ተፈራ
በ19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከዓለም 6ኛ ሆኖ ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ ቡድን ወደ ሀገሩ ሲመለስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል

በደማቁ የአቀባበል መርሀ ግብር ላይም የቡድኑን ቆይታ እንዲሁም የተገኘውን ውጤት የተመለከተ ንግግር ተደርጓል። ቡድኑን በመምራት ወደ ቡዳፔስት ያቀናው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ገዛኸኝ አበራ፤ ለብሔራዊ ቡድኑ ለተደረገው አቀባበል ምስጋናውን አቅርቧል። ለአንድ ወር ተኩል ያህል ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ በውድድሩ የተሳተፈው ቡድን ያስመዘገበው ውጤት ሕዝቡ ከለመደውና አምና ከተገኘው ውጤት አንጻር ያነሰ ቢሆንም ከሌሎች ሀገራት አንጻር ሲታይ ግን ጥሩ የሚባል መሆኑን ገልጿል። ከ34-35 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በሚደርስ ሙቀት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ውጤት ማግኘት ቢቻልም፤ በሚጠበቁትና እንደ የ5ሺ ሜትር ባሉት ርቀቶች ደግሞ ውጤት አለመገኘቱ ቅር የሚያሰኝ መሆኑን ጠቁሞ፤ አትሌቶቹ ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውን አስታውሷል። በዚህም ሕዝቡ ባይረካም በመጪው ኦሊምፒክ ግን የሚካካስ መሆኑን ቃል ገብቷል።

የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ፣ ቡድኑ ውድድሩን በጥሩ ሁኔታ ጀምሮ ስለማጠናቀቁ ጠቁማለች። እንደ ደራርቱ ገለፃ፣ አስቀድሞ የታቀደው ከአምናው ያነሰ ውጤት ላለማምጣት ነበር። በአትሌቶቹ ጥረትም ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የብሔራዊ ቡድን አትሌቶች የሏትም። ነገር ግን አትሌቶች በግላቸው በሚያደርጉት ጥረት እንዲሁም ውድድሩ ሲቃረብ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ በሚደረግ ዝግጅት ሀገራቸውን ይወክላሉ። ይህ የራሱ ተጽዕኖ ቢኖረውም ብሔራዊ ቡድኑ ግን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት እና በስፖርታዊ መርሆች በመመራት ውድድራቸውን በማጠናቀቃቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ለፓሪሱ ኦሊምፒክ ደግሞ ውጤቱ የሰመረ እንዲሆን ከወዲሁ ተጋግዞ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግራለች።

ሁሉም አሸናፊ ለመሆን በሚወዳደሩበት መድረክ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ በመሆናቸው እንኳን ደስ አላችሁ በማለት መልዕክታቸውን ያስተላለፉት ደግሞ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ ናቸው። አትሌቶች በቡዳፔስት ያለውን ከፍተኛ ሙቀት በመቋቋም እዚህ በመድረሳቸውም ክብር እንደሚገባቸው ተናግረዋል። መጪው ኦሊምፒክ እንደመሆኑም ኢትዮጵያ ከምትሳተፍባቸው የተለያዩ ስፖርቶች መካከል መገለጫዋ በሆነው አትሌቲክስ ከወዲሁ ሰፊ ዝግጅት ይደረጋል። ኮሚቴው ከሚያደርገው ዝግጅት ባለፈ መንግሥትም አትሌቶች በልዩ ሁኔታ የሚደገፉበትን እንዲሁም አስቸጋሪ የሆነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አለመኖር እንዲቀረፍ ሊሠራ እንደሚገባም ጠቁመዋል። በተጨማሪም በኦሊምፒኩ ላይ በመላው አውሮፓ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ቡድኑን ለመደገፍ ፓሪስ ላይ እንዲገኙ ለማድረግ እየተሠራ በመሆኑ መንግሥት ድጋፍ እንዲያደርግላቸውም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጀላ መርዳሳም የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። ‹‹አትሌቶች ያደረጉት ተጋድሎ አስደናቂ ነበር፤ በዚህም ሀገራቸውን በማስጠራታቸው ምስጋና ይገባቸዋል። የተገኘው ውጤትም የሚናቅ ሳይይሆን አጥጋቢ ሊባል የሚችል ነው። በተለይ ሴት አትሌቶች ለውጤት ያደረጉት አስተዋጽኦ አኩሪ ነው።›› በማለት ሴቶች ጠንካራና ኃላፊነትን የመሸከም አቅማቸው የታየበት መሆኑንም አንስተዋል። ለቡድኑ አባላት በቅርቡ የዕውቅና መድረክ እንደሚዘጋጅም ሚኒስትሩ ቃል ገብተዋል።

